# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 291 ሰኔ 21 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


## «ሰሞኑን በኦሮሚያ ክልል አረመኔያዊ ድርጊት የፈጸሙት ብሔርም ሆነ ሃይማኖት የሌላቸው ተላላኪዎች ናቸው»

- አቶ አደም ፋራህ
የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- ሰሞኑን በኦሮሚያ ክልል በንጹሃን ዜጎች ላይ አረመኔያዊ ድርጊት የፈጸሙት ወንጀለኞች ብሔርም ሆነ ሃይማኖት የሌላቸው ተላላኪዎች ናቸው ሲሉ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ተናገሩ።

አቶ አደም ፋራህ ትናንት በሰጡት መግለጫ፤ የአረመኔያዊ ድርጊት ፈጻሚዎችም ሆኑ የላኪዎቻቸው አላማ አንድም በብሔርና በሃይማኖት ሽፋን ሀገር ለማተራመስ ነው ብለዋል።

ከዚህ ባለፈ በቅርቡ የሚጀመረውን የህዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዙር ውሃ ሙሌትና የሁለተኛ ተርባይን ሥራ ጅማሮ ማስተጓጎል የጥፋት ቡድኖቹ አላማ እንደሆነ ተረጋግጧል ሲሉ ተናግረዋል።

ንጹሃን ላይ ጥቃት የፈጸሙት በርካታ የሸብር ቡድኑ አባላት ላይ አስፈላጊው ርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ገልጸዋል።

በዚህም ህይወታቸውን ያጡና በአካል የተያዙ የሸብር ቡድን አባላት መኖራቸውን ጠቁመው፤ ከተያዙት መካከልም የተለያየ ማንነትና የዕምነት ስርዓት ያላቸው

«ሰሞኑን በኦሮሚያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የሰሜኑን ጦርነት በሰላማዊ ሂደት ለመፍታት ፓርቲው ሦስት የመርህ ማዕቀፎችን አስቀመጠ

### - የሰላም ጥረቱ የማይሳካ ከሆነ ርምጃ ለመውሰድ እንደሚገደድ አስታውቋል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የሰሜኑን ጦርነት በሰላማዊ ሂደት ለመፍታት የብልጽግና ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ሶስት የመርህ ማዕቀፎችን አስቀመጡ። የሰላም ጥረቱ የማይሳካ ከሆነ ግን ትንኮሳዎችን ለመመከት አስፈላጊውን ርምጃ ለመውሰድ እንደሚገደድም አስታውቀዋል፡፡

የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ ትናንትና በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች የሰሜኑን ጦርነት በሰላም ሂደት መፈታት እንዳለበት ሰሞኑን ባደረጉት ስብሰባ ወስነዋል።

የሰላም ሂደቱ ሲከናወን ግን ሦስት ዋና ዋና የመርህ ማዕቀፎችን በተከተለ መንገድ ይሆናል በሚል ስምምነት መደረጉን የጠቆሙት ዶክተር ጌዲዮን፤ የመጀመሪያው መርህ የሰላም ሂደቱ ስምምነት ማንኛውንም ህገመንግስታዊ ድንጋጌዎችንና ህግጋትን ያከበረ መሆን እንዳለበት ውሳኔ እንደተሰጠበት ገልጸዋል።

በሁለተኛ ደረጃ በሰላም ሂደቱም ሆነ ውጤቱ የአገርን መሰረታዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ እንዲሆን ኮሚቴዎቹ አጽንኦት መስጠታቸውን የጠቀሱት ዶክተር ጌዲዮን፤ በሦስተኛ ደረጃ ሰላማዊ ሂደት የሚከናወን ከሆነ ሂደቱን



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

ማሳለጥ ያለበት የአፍሪካ ህብረት መሆን እንዳለበት መወሰናቸውንም ገልጸዋል።

ችግሮቻችንን ቢያንስ በራሳችን ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች መፍታት ነበረብን ያሉት ዶክተር ጌዲዮን፤ ጉዳዩ ግን ከእነሱ በላይ ከሆነ ቢያንስ ኢትዮጵያ ራሷ ባቋቋመችው የአፍሪካ ህብረት በኩል መከናወን እንዳለበት አቋም መያዙን አስታውቀዋል።

በዚህም የሰላም ሂደቱም ሆነ ውጤቱ ህገመንግስታዊ ድንጋጌዎችን በተከተለ እና የሀገርን ጥቅም በሚያስከብር መልኩ በአፍሪካ ሕብረት በኩል እንደሚከናወን ይጠበቃል ሲሉ አስረድተዋል።

ከዚህ ቀደም የሰላም አማራጮችን የሚያጠና ኮሚቴ ተዋቅሮ ጥናት ሲያደርግ እንደነበር ያስታወሱት ዶክተር ጌዲዮን፤ የጥናት ውጤቱ ሪፖርት መቅረቡንም አስታውቀዋል።

ሪፖርቱን ያዳመጠው የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፤ በአገሪቷ ሰሜናዊ ክፍል ያለውን ግጭት በሰላማዊ መንገድ መፍታት እንደሚያስፈልግ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ውሳኔውን የሚከታተል ኮሚቴ ማዋቀሩን ጠቁመዋል።

የሰላም ሂደቱም ተጨማሪ ደም መፋሰስ እንዳይከሰት፣ የተጀመረው የሀገራዊ ምክክር ሁሉን አካታች እንዲሆንና በጦርነቱ የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለማቋቋም እንደሚረዳ በማመን ፓርቲው ለወሰነው የሰላም ሂደት ውሳኔ መነሻነት እንደተጠቀመበትም አስረድተዋል።

የሰሜኑን ጦርነት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




አርሾ
ሜዲካል ላቦራቶሪ ኃ.የተ.የግ.ማ
ARSHO MEDICAL LABORATORIES PLC
በትውልድ የታመነ!
አድራሻ - አራት ኪሎ፣
ከአራዳ ክፍለ ከተማ ሕንፃ ጀርባ፣
የ24 ሰዓት አገልግሎት
612
0114-16-70-89
0911-10-18-18




## ወጣቶች ታሪካዊ አሻራቸውን ለሚያሳርፉበት የክረምት በጎ ፈቃድ ሥራ እንዲዘጋጁ ጥሪ ቀረበ

ገጽ 4


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ኩልሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

UNIC ETHIOPIA
ሕብረት ኢንሹራንስ አማ
THE UNITED INSURANCE COMPANY SC
Tomorrows Company Today'
ለህይወት
ሁሉም የመድን ፍላጎትዎ
ህጋዊ ግዴታዎ
ለንብረት
+251 111 26 34 34
united.insurance@unic-ethiopia.com
7469

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
MINISTRY OF TRANSPORT AND LOGISTICS

# ከቀረጥ ነጻ የገቡ ተሽከርካሪዎች ልዩ ሰሌዳ እንዲስጥፉ ሚኒስቴሩ አሳሰበ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ለአካል ጉዳተኛ ዜጎች ከቀረጥ ነጻ የገቡ ተሽከርካሪዎች የለጠፉትን ሰሌዳ በመመለስ አዲሱን ልዩ ሰሌዳ መለጠፍ እንዳለባቸው የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የሚኒስቴሩ የሕዝብ ግንኙነትና የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ አቶ ታጠቅ ነጋሽ ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ መንግሥት አካል ጉዳተኞች በትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የሚደርስባቸውን እንግልት ለመቅረፍ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ አስገብተው ለራሳቸው ብቻ እንዲጠቀሙ መመሪያ ቁጥር 41/2007 አውጥቷል።

በመመሪያው ድንጋጌ መሠረት እነዚህ ተሽከርካሪዎች ለታለመላቸው አገልግሎት እንዲውሉ አሁን የለጠፉትን ነባር ሰሌዳ በመመለስ አዲሱን ልዩ ሰሌዳ መለጠፍ እንዳለባቸውም ስራ አስፈጻሚው ጠቁመዋል።

መመሪያው ተጠቃሚዎች ከቀረጥ ነጻ ያስገቧቸው ተሽከርካሪዎች ልዩ ሰሌዳ እንዲሰጣቸው እንደሚደነግግ ያስታወሱት አቶ ታጠቅ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል ብለዋል።

ከመመሪያው ድንጋጌዎች አንዱ የመብቱ ተጠቃሚዎች ዓለም አቀፍ አካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪዎች መለያ ያለበት ሰሌዳ ብቻ መጠቀም መሆኑን ያስታወሱት ሥራ አስፈጻሚው፤ ይህም ተጠቃሚዎች ተሽከርካሪዎችን ሊገለገሉ በሚሄዱባቸው ነዳጅ ማደያ፣ መኪና ማቆሚያዎችና ሌሎችም ተቋማት በሚጓዙበት ወቅት የሚፈልጉትን አገልግሎት ቅድሚያ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል ብለዋል።

አሁን ላይ በተግባር የሚስተዋለው ከቀረጥ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎች አዲሱን ልዩ ሰሌዳ እየተጠቀሙ እንዳልሆነ ያስታወቁት ኃላፊው፤ ይህም አካል ጉዳተኞች ሊያገኙ የሚገባቸውን አገልግሎትና እገዛ እንዳያገኙ እንቅፋት ሆኗል። መንግስትም ተገቢውን ታክስና ቀረጥ እንዳያገኝ እያደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

አዲሱ ሰሌዳ መንግሥት የቀረጥና ታክስ ገቢውን ትቶ ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ የፈቀደላቸው ዜጎች ብቻ እንዲጠቀሙባቸው ለማድረግም እንደሚያግዝ አመልክተው፤ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ከተደረገ በኋላ በሕገወጥ መንገድ ለሶስተኛ ወገን በማስተላለፍ ተሽከርካሪዎችን ላልተፈለገ ዓላማ እንዲውሉ የሚያደርጉ ዜጎች አሉ ብለዋል።

በመሆኑም የመብቱ ተጠቃሚዎች ከሰኔ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ውስጥ የለጠፉትን ሰሌዳ መልሰው አዲሱን ሰሌዳ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ልዩ ሰሌዳውን ያልወሰዱ ተሽከርካሪዎች የሶስተኛ ወገን መድን ሽፋን፣ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ አገልግሎት (ቦሎ) እንደማያገኙ ገልጸው፤ የአዲስ አበባ ትራፊክ ፖሊስ፣ ፌዴራል ፖሊስ፣ ትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎችና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ልዩ ሰሌዳውን ያለጠፉ ተሽከርካሪዎች በቁጥጥር ስር እንደሚያውሉም አቶ ታጠቅ አስታውቀዋል።

አገልግሎቱ ለጊዜው በአዲስ አበባ ከተማ መሰጠት እንደሚጀምር ጠቅሰው፤ በቀጣይ በሁሉም ክልሎች ተመዝግበው የሚገኙ ከቀረጥ ነጻ የገቡ ተሽከርካሪዎች ላይ ይተገበራል ብለዋል።

እስካሁን ድረስ ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት እንዲውሉ ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር የገቡ 1700/ ከአንድ ሺ ሰባ መቶ/ በላይ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን መረጃዎች ያሳያሉ።




# «የአሸባሪዎች ፍላጎት እና ጥፋት የሁለቱን ሕዝቦች አንድነት ሊሸረሽረው አይችልም»

*- የአማራና የኦሮሚያ ክልሎች ርዕሳነ መስተዳድሮች*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የአሸባሪዎች ፍላጎት እና ጥፋት የሁለቱን ሕዝቦች አንድነት ሊሸረሽር እንደማይችል የአማራ እና የኦሮሚያ ክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች ገለጹ። የሁለቱ ክልሎች ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ዙሪያ ውይይት አድርገዋል።

የአማራ ክልል ርእሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ሰሞኑን በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ጊምቢ ወረዳ የተጨፈጨፉትን ንጹሐን ወገኖች በመጀመሪያ የኦሮሚያ ክልል ነዋሪዎች ቀጥሎ ኢትዮጵያዊ ናቸው፤ ይህን ደግሞ በጋራ አውግዘናል ነው ያሉት።

ሸኔ የአማራ ብቻ ጠላት አለመሆኑንና የጋራ የኢትዮጵያውያን ጠላት እንደሆነ የጠቀሱት ዶክተር ይልቃል፤ ሸኔን ከማጥፋት ውጪ አማራጭ እንደሌለ ተወያይተናል፤ አቅጣጫም አስቀምጠናል ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት ጦርነት እየጎሰመ ነው ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ ይህንንም መመከት የምንችለው በጋራ ነው ብለዋል።

የኦሮሚያ ክልል ርእሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ፤ ከዚህ በፊት የሁለቱ ሕዝቦች አብሮነት እየተገመደ እንጂ እየላላ አልሄደም፤ አሸባሪው ሕወሓት ሲነሳ አንድነታችን ጠንክሮ በአንድ ጉድጓድ እንደተቀበርን አሸባሪው ሸኔ ሲነሳም አንድነታችን የበለጠ እንዲጠናከር አድርጎታል ብለዋል።

ሸኔ ጊምቢ ላይ ጥቃት የፈፀመው ሦስት ዓላማዎችን ይዞ ነው ያሉት ርእሰ መስተዳድሩ፤ አንደኛ የአማራና የኦሮሞ ሕዝብን ለመለያየት ሲሆን፤ ይህ ትናንት ሕወሓትም አስቦ ያልተሳካለት ሸኔም ዛሬ የማይሳካለት በእኛ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም የማይሆን ነው ብለዋል።

ሁለተኛው ፍላጎታቸው ፍርሐትን በሀገሪቱ ማንገስ ሲሆን፤ ሦስተኛው ደግሞ ማሸበር ነው ብለዋል። ይህ እንዳይሳካ በጋራ ርምጃ እየወሰድን ነው ብለዋል።

ሁለቱ ሕዝቦች ትናንትም ዛሬም በጋራ መቆም እንደሚቻል ያሳዩ በመሆኑ ሸኔን መዋጋት አይከብዳቸውም ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ።

ዛሬ አንድነታችንን የምናሳየው ጽንፈኝነትን በመዋጋት ነው ያሉት አቶ ሽመልስ፤ ለሕዝባችን ለዓላማችን ስንል ትናንት መስዋእትነት እንደከፈልነው ነገም መስዋእትነት ከፍለን ኢትዮጵያን የተሻለች ሀገር እናደርጋለን ብለዋል።

ሸኔን ሽፋንና መረማመጃ አድርገው በአመራሩ ላይ የሚዘምቱ አመራሩን ለመከፋፈል የሚጥሩ ኃይሎች ግን ፍላጎታቸው ፈጽሞ አይሳካላቸውም ብለዋል።

የሁለቱ ክልል የብልጽግና ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች አቶ ግርማ የሺጥላ እና አቶ ፍቃዱ ተሰማ በበኩላቸው፤ ትናንት ወያኔ እሳት እና ጭድ ናቸው ብሎ በአንድነታችን ቢሳለቅም በጋራ እንደጣልነው ሁሉ የመከፋፈል ዓላማ ያለውን ሸኔን በጋራ እናጠፋዋለን ብለዋል።



ከአሰላ ትምህርት ኮሌጅ ጋር



ፎቶ ገበሬ ገብሬ

ከደብረብርሃን ትምህርት ኮሌጅ ጋር

# የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የመምህራን ልማትን ቀዳሚው ተግባር አድርጎ እንደሚሰራ ቢሮው አስታወቀ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የመምህራን ዘርፍን ማልማት ቀዳሚው ተግባር አድርጎ እንደሚሰራ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቢሮው አራት ሺህ የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራንን በዲፕሎማ ለማሠልጠን ከደብረብርሀን እና አሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ጋር ስምምነት አድርጓል።

ቢሮው በቅዳሜና እሁድ እና በክረምት መርሀ ግብር አራት ሺህ የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራን ለቀጣይ ሶስት አመት ለማሰልጠን ከኮሌጆቹ ጋር መፈራረሙን ኃላፊው አስታውቀዋል።

አቶ ዘላለም በመርሀ ግብሩ ባስተላለፉት መልዕክት የመምህራንን አቅም ማጎልበትና በተለያዩ ሥልጠናዎች ማብቃት የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ አንዱ ተግባራት ነው ብለዋል።

በአዲሱ ስርዓተ-ትምህርት የመምህራንን የትምህርት ደረጃ ከሰርተፊኬት ወደ ዲፕሎማ ማሳደግ በእርከኑ የተቀመጠውን ደረጃ ለማሟላት እና የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመምህራን እጥረት ለመቅረፍ እንደሚረዳ አስታውቀዋል።

የትምህርት ዕድሉን ያገኙ ሰልጣኝ መምህራን መርሃ ግብሩን በአግባቡ ተከታትለው በማጠናቀቅ ህጻናቱ ማግኘት የሚገባቸውን ዕውቀት ማስጨበጥ እንደሚጠበቅባቸውም ኃላፊው አሳስበዋል።

ኮሌጆቹም ቢሮው ያቀረበውን ጥያቄ ተቀብለው መምህራኑን ለመቀበል በመቻላቸው አመስግነዋል።

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት እጩ መምህራኑ ጨቅላ ህጻናት ትውልድን ከመሰረቱ በማብቃት የትምህርተ ጥራትን ለማረጋገጥ ወሳኝ በመሆኑ ልዩ ትኩረት እንዲጣቸው አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ በበኩላቸው፤ የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራኑ የዕድሉ ተጠቃሚ መሆናቸው ህጻናቱ ጥራቱን የጠበቀና እድሜያቸውን ያማከለ ትምህርት እንዲያገኙ ከመርዳቱም ባሻገር፣ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚያዘጋጃቸው መሆኑን አስገንዝበዋል።

ለስልጠናው በ11ዱም ክፍለ ከተሞች ከ5600 በላይ እጩ መምህራን መመዝገባቸውን ገልፀው፤ እነዚህ በውድድር ለሚያልፉ አራት ሺህ የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራን እድል እንደሚሰጥም ጠቁመዋል። ለዚህም 90 ሚሊየን ብር ሀብት የተመደበ መሆኑን ጠቅሰዋል።

እጩ መምህራኑን በቅዳሜና እሁድ እና በክረምት ለ3 ዓመት ለማስተማር የሚያስችለውን ስምምነት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ከኮሌጆቹ ተወካዮች ጋር ተፈራርመዋል።

ከኮሌጆቹ በኩልም የደብረብርሀን መምህራን ትምህርት ኮሌጅን በመወከል ረዳት ፕሮፌሰር መባህ ፈጠነ 2 ሺህ 500፤ እንዲሁም አሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅን በመወከል ረዳት ፕሮፌሰር ጎሳ ግርማ 1 ሺህ 500 የቅድመ መደበኛ ትምህርት እጩ መምህራኑን ለማስተማር የስምምነት ውሉን ተፈራርመዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንግሥት ትምህርት ቤቶች ቅድመ መደበኛ ትምህርት 252 ሺህ 864 ተማሪዎች እና 5120 መምህራን ይገኛሉ።

ዜና

# «ክህሎት የተላበሰ አመራርና ባለሙያ ማፍራት ወቅቱ የሚጠይቀው ወሳኝ ተግባር ነው»

**- ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር**
**የአዲስ አበባ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ**

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የጀመረችውን የለውጥ ጉዞ በማፋጠን በአገልጋይነት መንፈስ የተቃኘ የአመራር ጥበብና ክህሎት የተላበሰ አመራርና ባለሙያ መገንባት ወቅቱ የሚጠይቀው ወሳኝ ተግባር ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ተናገሩ።

የአዲስ አበባ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤና የአካዳሚው ሰብሳቢ ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ "ጠንካራ የከተማ አመራር ለአገራዊ ለውጥ፣ ዘላቂ ሰላምና ልማት" በሚል መሪ ቃል ሁለተኛውን አገር አቀፍ የጥናትና ምርምር ጉባኤ ባካሄደበት ወቅት ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የጀመረችውን የለውጥ ጉዞ ለማፋጠን እንዲሁም የህዝቡን ብልጽግና ለማረጋገጥ በየስትራቴጂክ ዘመኑ አገራዊና ተቋማዊ ልማትና የመልካም አስተዳደር ግቦችን የሚያሳካ፣ በአገልጋይነት መንፈስ የተቃኘ፣ የአመራር ጥበብና ክህሎት የተላበሰ አመራርና ባለሙያ መገንባት ወቅቱ የሚጠይቀው ወሳኝ ተግባር ነው።

አፈ ጉባኤዋ፤ የአንድ አገር ልማት አስተማማኝነትና ዘላቂነት የሚመዘነውና ሁለንተናዊ ልማትን ማረጋገጥ የሚቻለው በሰው ሀይል ላይ በሚደረግ ተከታታይ የአቅም ግንባታ ሥራና ተያይዞ በሚመጣው የአስተሳሰብ ለውጥ እንደሆነ ተናግረዋል።

በዚህ ዙሪያ የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች ተፈላጊውን የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት አስቻይ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የላቀ ፋይዳ እንዳላቸውም አፈጉባኤዋ ጠቅሰዋል።

እንደ አፈ ጉባኤዋ ገለጻ፤ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የአፍሪካ መዲናና የታላላቅ አለም አቀፍና አገር አቀፍ ዲፕሎማቲክ ተቋማት መቀመጫ ከመሆኗ አንጻር በከተማዋ የሚፈለገው አገልግሎት ሰፊ ነው። ከአገልግሎት አሰጣጡ ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ችግሮችና ፈተናዎችም ውስብስብ ናቸው።

በመሆኑም ውስብስብና ተለዋዋጭ የአገልግሎት ፍላጎትን በአግባቡ ማስተናገድ የሚችል፣ ችግሮችን ሊፈታ የሚችል፣ ተመጣጣኝ አስተሳሰብ፣ እውቀት፣ ብቃትና ልምድ ያለው አለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ፣ አገራዊና ተቋማዊ ተጨባጭና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን በመረዳትና በመተንተን አቀናጅቶ የመምራትና የመፈጸም ብቃት ያለው አመራርና ባለሙያ ያስፈልጋል ነው ያሉት አፈጉባኤዋ።


ለዚህም በየደረጃው ያለውን አመራርና ባለሙያ በትምህርትና ሥልጠና ማጎልበት፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ የማማከር አገልግሎቶችን በመስጠት የተቋማትን አሰራርና አደረጃጀት ለማዘመን የምርምር ጉባኤዎች ሚና የጎላ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

የአካዳሚው ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ደሳለኝ ጴጥሮስ በበኩላቸው፤ ዓለም ከደረሰችበት ከፍተኛ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁለንተናዊ የልኅቀት የቴክኖሎጂ ደረጃ መድረስ እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ ኢትዮጵያን ተወዳዳሪና ተፎካካሪ የሚያደርጋት የብልጽግና ማማ ላይ ለመውጣት ከማንኛውም ሀብት በላይ ትልቁን ሚና የሚጫወተው በአመለካከቱ የበለጸገ የሰው ሀብት መሆኑን ገልጸዋል።

"ሀገር ያላትን እምቅ ሀብት ለማልማትና ህዝብን ከድህነት አረንቋ አላቀን ወደ ከፍታው ዘመን ለመሻገር፤ አለምን የምናይበት የአመለካከት መነጽር የቀየረ፣ እራሱን በእውቀት፣ በክህሎት የገነባና በሙያዊ ሥነ ምግባር የታነጸ፣ ተነሳሽ የሆነና ብሩህ ራዕይ ያለው ፈጻሚና አመራር ማፍራት ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው" ሲሉ ዶክተር ደሳለኝ ተናግረዋል።

የዛሬዋ አዲስ አበባ ከተማ የምትለማውና የምትመራው የአሁኑን ትውልድ ፍላጎት ብቻ ለማርካት አይደለም ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ቀጣዩንም ትውልድ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ሥራዎች እየተሰሩ እንዳለ አመላክተዋል።

በዚህም አካዳሚው በቀጣይ የከተማዋን ተግዳሮቶችና ተስፋ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በጥናትና ምርምር የመለየት ሥራ እያከናወነ መሆኑን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ በመንግስትና በግል ተቋማት የአመራሩንና የፈጻሚውን አቅም ለመገንባት የሚረዱና ለውሳኔ ጠቃሚ የሆኑ ተግባራት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው ብለዋል።



አቶ ሽፈራው ተሲሳ

## ኅብረተሰቡ ለጥገና ሠራተኞች ገንዘብ እናዋጣ ከሚሉ ደላሎች ራሱን እንዲጠብቅ አገልግሎቱ አሳሰበ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የኤሌክትሪክ ኃይል ሲቋረጥ ለሚጠግኑ ሰራተኞች ብር እናዋጣ ከሚሉ የሰፈር ደላሎች ህብረተሰቡ እንዲጠነቀቅ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አሳሰበ።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ በስሩ ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር ባደረገው የትውውቅ መድረክ ላይ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሽፈራው ተሊላ እንደገለጹት፤ ከኤሌክትሪክ አገልግሎት የጥገና ስራ ጋር ተያይዞ የሚፈጸም የሙስና ወንጀልን ለመከላከል ህብረተሰቡ የበኩሉን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

ከሙስናና በተለያዩ አካባቢዎች ላይ የኃይል መስመር ጥገና ለማካሄድ ጥረት ሲደረግ አንዳንድ ደላሎች ብር አዋጥተን እንስጣቸው በሚል ከህብረተሰቡ ላይ ገንዘብ እንደሚሰበስቡ መረጃው አለን ያሉት አቶ ሽፈራው፤ ይህ አግባብ አለመሆኑን አውቆ ህብረተሰቡ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

አብዛኛው ሰራተኛ ሌሊትም እየሰራ ህይወቱን ጭምር አደጋ ላይ ጥሎ የሚያገለግል ነው። ይሁንና ለጥገና ሲሄዱ በየሰፈሩ ገንዘብ የሚቀበሉ ሰራተኞች ሊኖሩ ይችላሉ። በመሆኑም ገንዘብ በህገወጥ መንገድ የሚቀበሉት አብዛኛውን ሰራተኛ የማይወክሉ በመሆናቸው ችግሩ ሲገኝ ርምጃ ይወሰዳል ብለዋል።

ማንኛውም ሰራተኛ የጥገና ስራ በተመደበበት ሁሉ በአገልግሎቱ ቅጥር ስር እስካለ ድረስ ከህብረተሰቡ ተጨማሪ ክፍያ መቀበል የለበትም ያሉት አቶ ሽፈራው፤ ይህን ወንጀል የሚያበረታቱና የእራሳቸውንም ጥቅም የሚያሯሩጡ ደላሎች ደግሞ ችግሩን መፍጠራቸውን አስረድተዋል።

በመሆኑም ህብረተሰቡ የኤሌክትሪክ አገልግሎቱ በህጋዊ መንገድ በደረሰኝ የጠየቃቸውን ክፍያ ካልሆነ በስተቀር በየሰፈሩ የሚጠየቁትን ገንዘብ መክፈል እንደማይኖርባቸው ዋና ስራ አስፈጻሚው ጠቁመዋል።

ተቋሙ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት መላውን የኢትዮጵያን ክፍል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ዕቅድ መያዙን የተናገሩት ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች ቁጥር እያደገ ሲመጣ የጥገናና ተያያዥ ስራዎችንም በአንድ ተቋም አቅም ብቻ መሸፈን እንደማይቻል ይታመናል ብለዋል።

በመሆኑም በቀጣይ ከአገልግሎቱ ጋር በተያያዘ የጥገናና ሌሎች ተጨማሪ ስራዎችን ለማከናወን ከተቋሙ ውጪ ባሉ ድርጅቶች ለማሰራት ወይም አውትሶርስ የሚደረጉ ስራዎች እንደሚኖሩ ጠቁመዋል።

## ውዥንብርና ከፋፋይ ሂደት ውስጥ የገቡ አካላት ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ግብረ ኃይሉ አሳሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**




አዲስ አበባ፡- በሽብር ኃይሎች ላይ የተጠናከረ እርምጃ እየተወሰደ ባለበት በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ውዥብርና ከፋፋይ ሂደት ውስጥ መግባት የለብንም ሲል የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፀጥታ እና ደህንነት የጋራ ግብረ ኃይል አሳሰበ።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፀጥታ እና የደህንነት የጋራ ግብረ ኃይል ትናንት በሰጠው መግለጫ እንዳመለከተው፤ የሽብር ኃይሎችን በሁሉም አካባቢ የመቆጣጠር እና ህግ የማስከበር ስራ እየተሰራ ባለበት በዚህ ወቅት አንድ መሆንና አሸባሪዎችን በጋራ መፋለም ሲገባን በተለያየ ውዥንብርና ከፋፋይ ሂደት ውስጥ መግባት በፍፁም አይኖርብንም።

በቅርቡ የጋምቤላ ነፃነት ግንባር (ጋነግ)፣ የጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅንቄ (ጉህዴን) እና የሸኔ አሸባሪዎች ተደራጅተውና ተቀናጅተው በጋምቤላ ከተማና አካባቢው እንዲሁም በጊምቢና ደምቢ ዶሎ ከተማ ጥቃት ለመፈፀም ሙከራ አድርገው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፀጥታ እና ደህንነት የጋራ ግብረ ኃይል ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር በመቀናጀት በወሰዱት እርምጃ የሽብር ቡድኖቹ በከፍተኛ ደረጃ እየተደመሰሱና ተፈጥሮ የነበረውም ችግር ተወግዶ አካባቢው ወደ ሰላማዊ እንቅስቃሴ እንዲመለስ ተደርጓል ያለው መግለጫው፤ ይሁን እንጂ የሽብር ቡድኖቹ በምዕራብ ወለጋ ዞን ጊንቢ ከተማ አካባቢ የሚገኝ ቶሌ ቀበሌ ላይ ሰላማዊ በሆኑና ምንም በማያውቁ ንፁሃን ህፃናትና ሲቪሊያን ላይ ጉዳት ማድረሳቸውንና በርካቶችንም መግደላቸውን አውስቷል።

ወያኔ ሀገር የማፍረስ እኩይ ዓላማውን በጦርነት ማሳካት ስላልቻለ በየቦታው ባደራጃቸውና ባስታጠቃቸው ተላላኪ ቡድኖች አማካኝነት የጅምላ ግድያ በተልዕኮ እየፈፀመና እያስፈፀመ እንደሚገኝ መግለጫው አመልክቶ፤ የዚህ ድርጊት ዋና ዓላማም ህዝብ በመንግስት ላይ ተስፋ ቆርጦ እንዲነሳና ሰላም እንዲደፈርስ ለማድረግ መሆኑን አብራርቷል።

በተለይ በአሸባሪው ሕወሓት ጁንታ ቡድን ፋይናንስ የተደረጉ ሚዲያዎችን በመጠቀምና እኩይ ዓላማቸውን ለማስፈፀም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት ለማደናቀፍ ተማሪዎችን በብሄርና በሃይማኖት በመከፋፈል ግጭት እንዲፈጠር ለማነሳሳት ሌት ተቀን አሸባሪዎች እየሰሩ መሆናቸውን የጋራ ግብረ ኃይሉ የደረሰበት መሆኑን የፀጥታ እና ደህንነት የጋራ ግብረ ኃይል መግለጫ ጠቁሞ፤ የጠላትን ሴራና አካሄድ ጠንቅቀን ካልተረዳንና እነርሱ በከፈቱልን ቦይና ወጥመድ ውስጥ የምንገባ ከሆነ ለውስጥና ለውጭ ጠላቶቻችን እኩይ ሴራ በራችንን እንደከፈትን ይቆጠራል ሲል አሳስቧል።

እነዚህ በዶላር የተገዙ ሚዲያዎች ከዚህ ቀደም በጎንደር ችግር ከመፈፀሙ አስቀድመው ህዝቡን በሃይማኖት ለመከፋፈል አጀንዳ ቀርፀው ሰላም ለማደፍረስና ግጭት ለማቀጣጠል ሲሰሩ መቆየታቸውን መግለጫው አስታውሶ፤ የተፈጠረውን ግጭት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች እንዲዳረስና የእምነቱን ተከታዮች ወደለየለት ሁከትና ብጥብጥ ለማስገባት ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። ሆኖም የጥፋት ተልዕኳቸው በህዝባችን የመቻቻል ባህል፣ አርቆ አስተዋይነት፣ ትዕግስት እና በፀጥታ ኃይሎቻችን ከፍተኛ ርብርብ መክሸፉን አስገንዝቧል።

''ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል እንዲሉ'' እነዚህ ሚዲያዎች ሰሞኑን እንደለመዱት ግጭት ለመቀስቀስ በዩኒቨርሲቲዎች ላይ ያነጣጠረ ግጭት ለማስነሳት «በአማራ ክልል ዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩ የኦሮሞ እና የሌሎች ብሄር ተማሪዎችን ለማጥቃት የተደራጀ የደህንነት ቡድን ወደ አማራ ክልል ተልኳል» የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል ያለው መግለጫው፤ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፀጥታ እና ደህንነት የጋራ ግብረ ኃይሉ ከራሱ በፊት ለህዝብና ለሀገር ህይወቱን እየሰዋ የህዝብን ሰላምና ደህንነት የሚጠብቅ ኃይል መሆኑ የሚታወቅ ሆኖ ሳለ የተፈጠረውን ክስተት ምክንያት በማድረግ በሽብርተኞች ላይ የተጀመረው ዘመቻ ተጠናክሮ እንዳይቀጥል የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ እንደሚገኙም ጠቅሷል።

በመሆኑም የዩኒቨርሲቲዎቹ ተማሪዎችና ማህበረሰብ የተከሰተውን ችግር ምክንያት በማድረግ ሆን ብለው ግጭት ለማነሳሳት እየተንቀሳቀሱ ያሉ የአሸባሪው ሕወሓት ጁንታ ቡድን ተላላኪዎችና ቅጥረኞች መኖራቸውን በመገንዘብ ከእነዚህ አሸባሪዎች ራሳቸውን በመጠበቅ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ግብረ ኃይሉ አሳስቧል።

ሆኖም ይሄንን ማሳሰቢያ ተላልፈው ከድርጊታቸው የማይቆጠቡ አካላትን የማይታገስና ጥብቅ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚገደድ መሆኑን ማስታወቁን መግለጫው አመልክቷል።

# ወጣቶች ታሪካዊ አሻራቸውን ለሚያሳርፉበት የክረምት በጎ ፈቃድ ሥራ እንዲዘጋጁ ጥሪ ቀረበ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ወጣቶች ታሪካዊ አሻራቸውን ለሚያሳርፉበት የክረምት ወራት በጎ አድራጎት ስራ ዝግጁ እንዲሆኑ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ጥሪ አቀረቡ።

የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን "በጎነት ለኢትዮጵያ ከፍታ" በሚል የ2014 ዓ.ም የክረምት ወራት የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎትና የወሰን ተሻጋሪ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መርሐግብርን ትናንት ሲያስጀምሩ እንደገለጹት፤ ወጣቶች ታሪካዊ አሻራቸውን የሚያሳርፉበት የክረምት ወራት በጎ አድራጎት ስራን ለማከናወን ዝግጁ መሆን አለባቸው።

የሀገሪቱን ሉአላዊነት ለመዳፈር የሚደረጉ የውስጥና የውጭ ጫናዎችን ለመመከትና ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ መንግስት እያከናወነ የሚገኘውን ሁለንተናዊ ጥረት ውጤታማ እንዲሆን በወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተግባራት መደገፍ እንደሚኖርበትም አቶ ደመቀ ተናግረዋል።

የተጀመረው የከፍታ ጉዞ የተሳካ እንዲሆን ወጣቶች የዜግነት ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ፣ ወጣቶች የክረምት ወራትን በጎ አድራጎት ስራን ለማከናወን ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው አስታውቀዋል።

የኢፌዴሪ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በበኩላቸው፣ የበጎ ፈቃድ መርሐ ግብር ወጣቶች በራሳቸው ተነሳሽነት፣ መልካም ፍቃድና ፍላጎት ተንቀሳቅሰው የህብረተሰቡን ማህበራዊ ትስስርና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ጥረቶች ለመደገፍ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ለማስቻል ያለመ ነው ብለዋል።

ህብረተሰቡም የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለሚያከናውኑ ወጣቶች አስፈላጊውን ትብብርና ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

በክረምቱ ወራት ብቻ በሚደረግ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት 19 ሚሊዮን ወጣቶችን በአስራ ሁለት የስምሪት መስኮች በማሰማራት 40 ሚሊዮን የሚጠጋ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ መታቀዱንና በዚህም 11 ቢሊዮን ብር የሚገመት ሀብት ለማዳን እቅድ መያዙን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማህበራዊ ጫናዎችን ከማቃለል ባለፈ ወጣቶች ሀገራቸውን እንዲያውቁና የማህበረሰቡን በጎ እሴቶች እንዲያውቁ ዕድል የሚፈጥርበት መሆኑንም አንስተዋል።

ባለፉት የበጋና የክረምት ወቅቶች በበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ከ21 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች ተሳትፈው ከ38 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ዜጎች 10 ቢሊየን ብር የሚገመት አገልግሎት መስጠታቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንንን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ በጎ ፍቃድ አገልግሎት ስኬታማ እንዲሆን ያላቸውን ቁርጠኝነት የሚያረጋግጡበትን ፊርማም በቃል ኪዳን ሰነዱ ላይ አኑረዋል።

# አገልግሎቱ የመድኃኒት ብክነትን ዜሮ ለማድረስ እየሠራ መሆኑን ገለፀ

ውብሸት ሰንደቁ



አቶ ሰሎሞን ንጉሴ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ የመድኃኒት ብክነትን ዜሮ ለማድረስ እየሠራ መሆኑን ገለፀ።

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰሎሞን ንጉሴ፤ የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት እና የክምችት ሁኔታዎችን በማሻሻል በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚከሰተውን የመድኃኒት ብክነትን ዜሮ ለማድረስ እየሠራ መሆኑን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም የነበረው የመድኃኒት አስተዳደር ሥርዓት ወጥ ባለመሆኑ ምክንያት መድኃኒቶች ተገዝተው ጥቅም ላይ እስከሚውሉበት ጤና ተቋም ድረስ ያለው ሂደት መድኃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው አልፎ የሚከሰተው የብክነት መጠን ከፍተኛ ነበር ብለዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በአንድ ሀገር ውስጥ የገባ መድኃኒት ተቀባይነት ያለው የብክነት መጠን ከሁለት በመቶ በታች እንደሆነ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፤ ቁጥሩ ከኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ጀምሮ እስከ ጤና ተቋማት ባሉ መጋዘኖች ሊኖር የሚገባው ተቀባይነት ያለውን የብክነት መጠን የሚያመላክት እንደሆነ ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ብቻ ከሁለት ዓመት በፊት የነበረው የብክነት መጠን ከሁለት በመቶ በላይ እንደነበርም ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አብራርተዋል።

በሀገር ደረጃ በጤና ተቋማት በጊዜ ማለፍና በሌሎች ምክንያቶች የሚባክነውን የመድኃኒት መጠን የሚያሳይ መረጃ እጃችን ላይ የለም ያሉት አቶ ሰሎሞን፤ ሆኖም በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ብቻ ከ2 ነጥብ 4 በመቶ በላይ የደረሰ የመድኃኒቶች ብክነት ይከሰት ነበር ብለዋል።

እንደ አቶ ሰለሞን ገለጻ፤ ይህ የብክነት መጠን በጤና ጣቢያዎች ከሚባክነው መድኃኒት ጋር ሲደመር በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካለው የብክነት መጠን ከፍተኛ ነው። በሀገሪቱ ላይም የሚያስከትለው የጉዳት መጠንም ከፍተኛ ነው።

ዝቅተኛና ተቀባይነት ያለው የብክነት መጠን እንዲኖር የአሠራር ሥርዓቶችን የመዘርጋት እና የክምችት ሁኔታዎችን የማሻሻል ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሆነም አቶ ሰለሞን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ሰለሞን ገለፃ፤ በተወሰዱት እርምጃዎች አሁን ባለው ሁኔታ በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት በኩል ያለው የመድኃኒቶች ብክነት ቀንሷል። ከሁለት ዓመት በፊት ከ2 ነጥብ 4 በላይ የነበረው የመድኃኒቶች ብክነት ወደ 0 ነጥብ 7 በመቶ ደርሷል። በጤና ጣቢያዎች ያለው ብክነትም ጥናት የሚያስፈልገው ቢሆንም እንደሚቀንስ ይታመናል።

የክምችትና አያያዝ እንዲሁም የሥርጭት ሥርዓት በመቀየሩም በርካታ መድኃኒቶችን ከብክነት መታደግ መቻሉንም አብራርተዋል። በግዢ ሥርዓትም ከዚህ ቀደም በዓመት አንዴ ይደረግ የነበረው ግዢን በመቀየር የማዕቀፍ ግዢ ሥርዓት ሊዘረጋ በመቻሉ ብክነቱን ዝቅ ለማድረግ አጋዥ መሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም በነበረው የግዢ ሥርዓት መድኃኒቶች በጅምላ ለአንድ ዓመት በአንዴ መገዛታቸው ለብክነት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደነበረው ያስታወሱት አቶ ሰለሞን፤ በአሁኑ ጊዜ የማዕቀፍ ግዢ ሥርዓት በመዘርጋቱ ለጥቂት ወራት የሚያስፈልገው መድኃኒት ብቻ ስለሚገዛ አንዴ ቀርቦ የሚበላሽ መድኃኒት አይኖርም። በዚህም ምክንያት የብክነት መጠን እንዲቀንስ መደረጉን አብራርተዋል።

በቀጣይም በመድኃኒት አቅራቢ የመድኃኒት ክምችት ውስጥ የሚከሰተው የመድኃኒት ብክነት ወደ ዜሮ በመቶ እንዲወርድ እየሠሩ መሆኑን የአገልግሎቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰሎሞን ተናግረዋል።

# «ሰሞኑን በኦሮሚያ...

ከገፅ 1 የዞረ

መገኘታቸውን ተናግረዋል።

አቶ አደም በመግለጫቸው፤ የሸብር ቡድኖቹን ፋይናንስ በማድረግና እኩይ አላማ በመስጠት የሚያሰማራቸው የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸው፤ እነዚህ ጠላቶች መቼም እንደማይተኙልን አሳይተዋል። ጥቃቱም ህዝብና መንግስትን ለማለያየት ያለመ ነው ብለዋል።

በተለይም በክረምት ወቅት በርካታ ህዝብ የሚሳተፍባቸውን የልማት ስራዎች ለማስተጓጎልና ትኩረት ለመሳብ ያለመ አሰቃቂ ጥቃት በንጹሃን ላይ መፈጸማቸውንም አቶ አደም ገልጸዋል።

ይህ አላማ እንዳይሳካ በንጹሀን ዜጎች ላይ እጅግ ዘግናኝና አረመኔያዊ ድርጊት ተፈጽሟል ያሉት አቶ አደም፤ የፓርቲያቸው ሥራ አስፈፃሚና ማዕከላዊ ኮሚቴዎች በአረመኔያዊ ድርጊቱ የተሰማቸውን ሀዘን መግለጻቸውን አስታውሰዋል።

ከጠላቶቻችን የፋይናንስ ድጋፍ አግኝተው አረመኔያዊ ድርጊቱን የፈጸሙት ተላላኪዎች ላይ የሚወሰደው የተጠናከረ ርምጃ እንዲጠናከር የብልጽግና ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች መወሰናቸውንም ተናግረዋል።



በተያያዘ ጽንፈኝነትን መከላከል ትኩረት የሚደረግበት ጉዳይ መሆኑን ፓርቲው ስምምነት ማድረጉን የገለጹት አቶ አደም፤ ጽንፈኛ ኃይሎች የዲጂታል ቴክኖሎጂውና የዲጂታል ኢኮኖሚውን መስፋፋት ተጠቅመው ችግር እየፈጠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከዚህ ባለፈ ኋላቀርነትና የዴሞክራሲ ጽንሰሃሳብ አለመስፋፋት ሀገሪቷን እየፈተነው ይገኛል ያሉት አቶ አደም፤ በመሆኑም መንግስት ጽንፈኝነትን በመከላከል ችግር ፈጣሪዎች ላይ ርምጃ ይወስዳል ብለዋል።

በሌላ በኩል ፓርቲው በአገሪቷ የዲፕሎማሲ ስራዎች ላይ ውይይት ማድረጉን አቶ አደም አንስተዋል። ኢትዮጵያ በርካታ የዓለም ኃያላን ሀገራት ትኩረት በሚያደርጉበት የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ እንደመሆኗ ፖለቲካዊ አካሄዶቿ ጥንቃቄ የተሞላበትና የሀገራችንን ጥቅም በሚያስከብር መልኩ የዲፕሎማሲ ስራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ስምምነት ተደርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ አደም ገለጻ፤ የዓለም የፖለቲካ ሽኩቻን በተመለከተ የሀገራችንን ጥቅም ከማስከበር ባለፈ ሚዛናዊ አካሄዶችን መከተል እንደሚገባ ውይይት ተደርጓል። የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ስራ ለማጠናከር በዋናነት የውስጥ ተጋላጭነትን በመቀነስ የተጀመረውን አካታች አገራዊ ምክክር መቀጠል እንደሚገባ ውሳኔ ላይ ተደርሷል።

# የሰሜኑን ጦርነት...

ከገፅ 1 የዞረ

ይሁንና የሰላም ሂደቱ በተፈለገው መንገድ የማይሳካ ከሆነና የሕወሓት ሽብር ቡድን የሚያደርገውን ትንኮሳ የሚቀጥል ከሆነ አስፈላጊውን ርምጃ ለመውሰድ ዝግጅት ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ፓርቲው መስማማቱን ዶክተር ጌዲዮን አስረድተዋል።

ለዚህም እንዲረዳ አስፈላጊውን ርምጃ ለማከናወን የሚመለከታቸው የመከላከያ ሠራዊት፣ የደህንነት ተቋማትና የጸጥታ አካላት አስፈላጊውን የጥንቃቄና የዝግጅት ስራ አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ፓርቲው ማሳሰቡን ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ጌዲዮን ገለጻ፤ የሰሜኑ ጦርነት መንግስት ተገዶ የገባበት ሲሆን፤ መንግስት በተደጋጋሚ ጊዜ ለሰላም ያለውን ፍላጎት ለማሳየት የተኩስ አቁም አድርጓል። በቀጣይም ለሰላም ሂደቱ መሳካት የሚያስፈልጉ አማራጮችን ሁሉ ይወስዳል። ይሁንና የሰላም ሂደቱ የማይሳካ ከሆነና ትንኮሳዎች ከቀጠሉ መንግስት ሕግ የማስከበር ስራውን አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የብልጽግና ፓርቲ ማዕከላዊና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ውሳኔ አሳልፈዋል።

በተያያዘ ዜና በፌዴራል መንግሥት በኩል የሰላም ተደራዳሪ ቡድን መሰየሙንና የቡድኑ አባላትም የሚከተሉት መሆናቸው ታውቋል።

1. አቶ ደመቀ መኮንን----------------ሰብሳቢ
2. ዶ/ር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ--------አባል
3. አቶ ተመስገን ጥሩነህ-------------- አባል
4. አምባሳደር ሀሰን አብዱልቃድር------አባል
5. አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን----------አባል
6. ሌ/ል ጄኔራል ብርሀኑ በቀለ----------አባል
7. ዶ/ር ጌታቸው ጀምበር -----------አባል

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕዝባችን ነገሮችን ከፍ ባለ ሃላፊነት የሚወጣበትን ስክነት መፍጠር ይጠበቅበታል

አሸባሪው ሕወሓት ከፍጥረቱ ጀምሮ ለሰላም እድል መስጠት የሚያስችል ማንነት የገነባ ድርጅት አይደለም። ከዚህ ይልቅ ከፍ ባለ ሴራ በንጹሃን ደምና በተስፈኞች ተስፋ እየነገደ እድሜውን ያስረዘመ ፤ ለሀገርና ለሕዝብ ጠንቅ የሆነ ድርጅት ነው። በዚህም ላለፉት 50 ዓመታት ገደማ በሀገርና በሕዝብ ላይ ያደረሰው ሁለንተናዊ ጥፋት የከፋ ነው።

ገና ከውልደቱ ጀምሮ ይዞት የተነሳው ሀገር አፍራሽ የፖለቲካ ሪእዮተዓለም እና የሴራ ፖለቲካ የትግራይን ሕዝብ ጨምሮ መላው ሕዝባችንን ያስከፈለው እና አሁንም እያስከፈለ ያለው ዋጋ ከፍ ያለ ነው። በዚህም ሀገር እንደ ሀገር ዜጎቿን እና ሀብቷን በከንቱ ለመገበር ተገዳለች።

በሥልጣን ዘመኑ ከጎረቤት ሀገራት ሕዝቦች ጋር ሳይቀር ግጭት በመፍጠር ሀገርን ዘግናኝ የሆነ ጦርነት ውስጥ ከቷል። በዚህም ሀገርና ሕዝብ የከፈለው ዋጋ ለትርክት የማይመች ፤ በታሪክ ውስጥ በጥቁር ነጥብነቱ የሚጠቀስ ነው። የጦርነቱ ትርጉም አልባነቱ ደግሞ ሀገርና ሕዝብን ከፍ ያለ የልብ ስብራት ውስጥ የከተተ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

"ጦርነት የባህል ጨዋታችን ነው" ብሎ የሚያስበውና ከዚህ በሚመነጭ እብሪትና ማን አለብኝነት የተገነባው የቡድኑ ያልተገባ ሥነልቦና በየወቅቱ እንደ ሀገር ያጋጠሙንን ችግሮች በሰላማዊ መንገድ በመነጋገር ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶችን ፍሬ አልባ አድርጓል። ስለ ሰላም መዘመርን እንደ ሽንፈት አድርጎ በመውሰዱም ሀገርና ሕዝብን ያልተገባ ዋጋ አስከፍሏል ፤ እያስከፈለም ይገኛል።

ሁልጊዜ ለጥፋትና ለሴራ የሚያደባው ቡድኑ በሥልጣን በነበረባቸው ጊዜያት ሳይቀር ከራሱ አልፎ በአምሳያው የተለያዩ አሸባሪ የጥፋት ቡድኖችን በመፍጠርና የፖለቲካ እውቅና በመስጠት የሀገርን አንድነትና የሕዝቦችን ተቻችሎና ተከባብሮ የመኖር የቆየ እሴት ሸርሽሯል። በዚህም በሕዝቦች መካከል አለመተማመንና መጠራጠር እንዲሰፍን ብዙ ሰርቷል።

በተለይም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ "ሀገርን ለማፍረስ እስከ ሲኦል እንሄዳለን" በሚል እየሄደበት ያለው የጥፋት መንገድ ፤ ቡድኑ የቱን ያህል ለሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ችግሮች ሰላማዊ የድርድር መንገዶችን ለመቀበል የሚያስችል ፍጥረታዊ ስብእና እንደሌለው በተጨባጭ ያመላከተ ነው።

በወቅቱ የተከሰቱ አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሀገር ሽማግሌዎችን ፤በግጭት ጊዜ ዋነኛ የጥቃት ተጋላጭ የሆኑ እናቶችን ጨምሮ ሌሎች ለሰላም ግንባታ አቅም የሆኑ አማራጮችን በመጠቀም መንግሥት ላደረጋቸው ጥረቶች ተገቢውን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በጥረቶቹ ሲያፌዝ እና ሲያላግጥ ተስተውሏል።

ይህንኑ ተከትሎ በከፈተው ጦርነት በመቶ ሺ የሚቆጠሩ የትግራይ ወጣቶችን በመገበር ምንም አይነት ሰብአዊነት የሌለው ፤ ለሥልጣን ሲል የትኛውንም ክፋትና ውድመት ለመፈጸም ወደ ኋላ እንደማይል በተግባር አሳይቷል። በከንቱ ስለፈሰሰው የትግራይ ወንድሞቻችን ደም ከመጸጸት ይልቅ፤ ለሌላ የጦርነት እልቂት የትግራይን ወጣት ለማሰለፍ ደፋ ቀና ሲል እየታየ ነው።

ይህ ከጅምሩ በንጹሃን ደምና በሴራ ፖለቲካ ጥርሱን የነቀለውና ይህንንም የማንነቱ ትምክህት አድርጎ የሚቆጥረው አሸባሪ ሕወሓት ፤ ዛሬም የሕዝባችንን ነገዎች ከግጭት ነጻ በማድረግ ከጦርነት አዙሪት ለመውጣት በመንግሥት በኩል የተዘረጋውን የሰላም እጅ ለማሳጠፍና ዳግም ሀገርና ሕዝብን በጦርነት ዋጋ ለማስከፈል ፉከራና ቀረርቶ ውስጥ ይገኛል።

በአንድ በኩል የሰላም ሀዋሪያ ለመምሰል በተለይም ለዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ የሰላም ዜማዎችን እያዜመ፣ በሌላ በኩል መያዣ ያደረገውን የትግራይ ሕዝብ ባልተገባ የጥላቻ ትርክትና በግድ ወደ ጦርነት ለማስገባት ሰፊ ቅስቀሳ እያደረገ ነው። ይህ ብድን እየመረጠው ያለው የጥፋት መንገድ የከፋ ዋጋ እንዳያስከፍለን ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

በተለይም መላው ሕዝባችን በየቦታው የሚፈጠሩ ግድያዎችና መፈናቅሎች በአንድም ይሁን በሌላ የዚህ ቡድን የሴራ ስሪት መሆኑን ተረድቶ በቡድኑ የሴራ መረብ ተጠልፎ እንዳይያዝ እና እንዳይወድቅ ከስሜታዊነት እራሱን ማራቅና ፤ ነገሮችን ከፍ ባለ ሃላፊነት የሚወጣበትን ስክነት መፍጠር ይጠበቅበታል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# አሸባሪው ሕወሓትና የመኸር ወራት ጦርነት?

**ሜላት ኢያሱ**

የመኸሩ ወራት የአገራችን አርሶ አደሮች ዘገር የሚጨብጡበት ሳይሆን እርፍ ጨብጠው የዓመት ጉርሳቸውን ለማምረት ደፋ ቀና የሚሉበት ነው። በተለይም የትግራይ አርሶ አደሮች የእርዳታ ስንዴ ጥገኛ ላለመሆን የመኸሩን ወቅት በሥራ የሚያሳልፉበት ሊሆን በተገባ ነበር። የሕወሓት አሸባሪ ቡድን ግን የመኸሩን ወቅት ለጦርነት የመረጠው ይመስላል።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በዙሪያው ያሉ አርሶአደሮችን ወደ ጦርነት እየመለመለ ለማስገባት ከሚጠቀምበት ስልት አንዱ ረሃብ ነው። አስቀድሞ ረሃብ እንዲፈጠር የተለያዩ አሻጥሮችን ይሠራል። ከአሻጥሩ አንዱ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎችና በዙሪያ ገባው ጦርነት በመክፈት ምርት እንዳይመረት ማድረግ ነው። ከዚያም ይህን ያህል ሕዝብ ለረሃብ አደጋ ተጋልጧል እያለ ዓለምአቀፍ እርዳታ መሰብሰብ ነው።

በመቀጠልም በረሃብ ምክንያት ለምኖ የሚያገኘውን ርዳታ (ስንዴም ይሁን ገንዘብ) ቅድመ ሁኔታ እያስቀመጠ ለተጎጂዎች ይቆነጥርላቸዋል። እርዳታ የሚያደርግላቸው በረሃብ አደጋ ውስጥ ላሉት ሁሉ ሳይሆን የእርሱን ዓላማና ትግል ለሚደግፉ ብቻ ነው። ከዚያ በመቀጠል ከረሃብና ከችግር ለመውጣት ታግሎ ነጻ መውጣት አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደሆነ ይሰብካል።

ሰዎች ላለመራብና የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ሕይወት ለማትረፍ ሲሉ የሚቆነጠርላቸውን እርዳታ እየወሰዱ ሳይወዱ በግድ የጉዳዩ አስፈጻሚ ይሆናሉ።

ቡድኑ በበጋው ወራት ከሰበሰበው እርዳታ እየቆነጠረ ለጦርነት የመለመላቸውን ተዋጊዎች አሰልጥኖ በአፋር፣ በአማራና በኤርትራ አዋሳኝ አካባቢዎች በማስፈር ቀጣናውን ውጥረት የነገሰበት አድርጎ መሰንበቱ የሚታወስ ነው። አሁን ደግሞ በአካባቢው ያሉ አርሶ አደሮች አምርተው እንዳይጠቀሙ የመኸሩን ወቅት ጠብቆ የግብርናውን ሥራ ለማስተጓጎል እየተዘጋጀ ይገኛል። ትንኮሳዎችንም እያደረገ ነው።

ሕዝብ በረሃብ አንገቱን እንዲደፋ፣ ችግሮች እንዲባባሱ፣ እንዳይታረስ፣ እንዳይመረት፣ የተፈናቃዮች ቁጥር እንዲጨምር፣ መንግሥት ተፈናቃዮችን በመርዳት እንዲወጠር ለማድረግ አልሞ እየተንቀሳቀሰ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በትግራይና በአጎራባች አካባቢዎች የሚኖሩ አርሶ አደሮች እየተለመነ በሚመጸውታቸው እፍኝ የማይሞላ ስንዴ የእርሱ ተገዢ እንዲሆኑ የነደፈው አንድ ስትራቴጂ መሆኑን ከቀደመ ልምዱ መረዳት አይከብድም።

የመንግሥት የልማትና የእድገት ስትራቴጂዎች ግባቸውን እንዳይመቱ ማድረግ ሌላው ዓላማው ነው። ኢትዮጵያ በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃግብር ትኩረት ከሰጠቻቸው አምስት የኢኮኖሚ ዘርፎች አንዱ ግብርና ነው። የግብርና ምርትን አስተማማኝና ተከታታይነት ባለው መንገድ ለማሳደግ እቅድ ተይዞ ወደ ሥራ ከተገባ ሁለትና ሶስት ዓመታት ተቆጥረዋል። በነዚህ ዓመታት በምግብ አቅርቦት ራስን ለመቻልና ከዚያም አልፎ የውጭ ምንዛሬ ለማምጣት የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች ተነድፈው አበረታች ውጤቶች መታየት ጀምረዋል።

ግብርናው ከመኸር ወቅት ሥራ ተላቆ በመስኖ የማምረት ባህል እንዲያዳብር በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። በተለይም ከውጭ የሚገባውን እና ከፍተኛ ምንዛሬ የሚጠይቀውን ስንዴ ለማስቀረት እየተደረገ ያለው የበጋ መስኖ ልማት ከፍተኛ ውጤት እየታየበት ነው።

27 ዓመት ሀገር ሲያስተዳድር በነበረ ጊዜ የእርዳታ ስንዴን እየለመነ የመመገብ ልክፍት የተጸናወተው አሸባሪው ቡድን ዛሬ ኢትዮጵያ የግብርናውን ምርታማነት ለማሳደግ ያሳየችው ጅምር ምቾት ስላልሰጠው አርሶ አደሩ እንዳያመርት በአንድ እጁ መሳሪያ ይዞ እየተዋጋው ሲሆን ሌላው እጁን ደግሞ እንደለመደው ለስንዴ እርዳታ ወደ ውጭ እየዘረጋው ይገኛል።

ባለፈው ሳምንት የአውሮፓ ሕብረት የአደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽነር ጃኒዝ ሌነርሲስ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ጋር ተወያይተዋል። ወደ መቀሌ ሄደው ከአሸባሪው ቡድን አመራሮችም ጋር ተመሳሳይ ውይይት ማድረጋቸው ይታወሳል።

የውይይቱ ዝርዝር ፍሬ ሃሳብ ባይገለጽም ኮሚሽነር ጃኒዝ ሌነርሲስ በተለይም ወደ ትግራይ ክልል የሚገባው እርዳታ መሻሻል እንደታየበት ተናግረዋል። በቀጣይም የፌዴራል መንግሥቱ የነዳጅ አቅርቦትና የጥሬ ገንዘብ እጥረት እንዲፈታ የበኩሉን ትብብር እንዲያደርግ ለጋዜጠኞች ከሰጡት መግለጫ መረዳት ተችሏል።

ይህ ሲታይ አሸባሪው ሕወሓት የሰላም መንገዶችን ለመከተል የተዘጋጀ ይመስል ነበር። ብዙም ሳይቆይ የአሸባሪው ቡድን ቃል አቀባይ ጌታቸው ረዳ በፌስቡክ ገጹ ካሰፈረው ጽሑፍ መረዳት የቻልነው ኮሚሽነር ጃኒዝ ሌነርሲስ እና ደብረጽዮን ገብረማርያም ገንቢ ውይይት ማድረጋቸውን ነው። ከአንድ ቀን በፊት ደግሞ መድሃኒትና ሌሎች ሰብአዊ እርዳታ ይዘው ወደ ትግራይ የሚበሩ አውሮፕላኖች ትግራይ ምድር ላይ እንዳያርፉ አስጠንቅቋል። ያም ብቻ ሳይሆን በሰሜን ወሎ የተወሰኑ ወረዳዎች ወረራውን በማስፋፋት ልክ እንደከርሞው የእርሻ ወቅቱን በማወክ ላይ ይገኛል።

ቡድኑ ከፌዴራል መንግሥት ጋር የመደራደር ፍላጎት እንዳለው አመራሮቹ በተለያዩ ጊዜያት ከሚያስተላለፉት መልእክት እንረዳለን። ሁኔታው ግን ከማስመሰል የዘለለ አይደለም።

ቡድኑ ሁልጊዜም የሰላም አማራጭን በማጣት ተገዶ ወደ ጦርነት እንደገባ ይናገራል። ፌዴራል መንግሥት በከበባ ውስጥ እንዳስቀመጠው፣ የመሰረተ ልማት አገልግሎት እንዳሳጣው፣ የእርዳታ እህል እንዳይገባ መተላለፊያ በሮች እንደተዘጉበት ይገልጻል። እንዲህ አይነት ዲስኩር የሚያደርገው ደግሞ ምእራባውያንን ለማታለል ብቻ ሳይሆን እራሱን የትግራይ ሕዝብን ጭምር ወደ ጦርነት ማስገባት ሲፈልግ እንደሆነ የቀደመው ልምዱ ይነግረናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን ለፓርላማ አባላት ባደረጉት ንግግር መንግሥት እስከ አሁን ድረስ ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር ምንም አይነት ድርድር አለመጀመሩን አስረድተው፤ ነገር ግን ችግሮችን በንግግርና በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት መንግሥታቸው ምን ጊዜም ዝግጁ እንደሆነ ተናግረዋል።

የመንግሥት እጆች አሁን ሳይሆን ገና ድሮ በዚህ መጠን ቀውስ ውስጥ ከመገባቱ በፊት ለሰላም የተዘረጉ መሆናቸው በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። የሰላም አምባሳደር እናቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች መቀሌ ድረስ በመሄድ ያቀረቡትን የሰላም ጥሪ ማስታወስ ያስፈልጋል።

ጦርነትን ባህላዊ ጨዋታው አድርጎ የሚመለከት ይህ ቡድን የሰላምና የእርቅ ፍላጎት እንዳለው እያስመሰለ ለጦርነት ሲዘጋጅ መክረሙ የሚያስገርመን ላይሆን ይችላል።

እውን አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ከመጀመሪያ ጀምሮ የሰላም አማራጭ አጥቶ ነው ወደ ጦርነት የገባው ወይስ በጦርነት የበላይነትን ወስዶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማንበርከክ የሚፈልግ የአምባገነኖች ስብስብ ስለሆነ ነው?

ቡድኑ የተንኮል ፊት አውራሪ፤ የበደል፣ የአሻጥር፣ የግፍና የጭካኔ መምህር ስለመሆኑ አምና እና ካቻአምና በአማራና በአፋር ክልሎች በንጹሃን ዜጎች፣ በእንስሳትና በእጽዋት ላይ ሳይቀር የፈጸማቸውን ግፎች ብቻ ማስታወስ በቂ ነው።

‹‹ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ›› እንዲሉ አሸባሪው ቡድን አሁንም ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሥነልቦና ዝግጅት ያለው አይመስልም። እንደለመደው ዘንድሮም የመኸሩን ወቅት ለጦርነት መርጦ ትንኮሳዎችን እያደረገ ይገኛል። የተጸናወተው የክፋት መንፈስ ጥሩ ነገር ስለማያሳስበው እንደ ከርሞው ሁሉ ዘንድሮም በዙሪያ ገባው የሚገኙ አርሶ አደሮችን አምርተው እንዳይበሉ ስጋት ደቅኖባቸዋል።

አሸባሪው ቡድን ላለፉት ዓመታት የእርዳታ ስንዴ (የምግብ እህል) ተማጽኖ ሲያደርግ ለሰማው የምግብ እህል እንዳይመረት እንቅፋት ይሆናል ብሎ አያስብም። እያመረቱ ለሕዝቡ መትረፍ ሚችሉት የትግራይ አርሶ አደሮች በልመና ከሚገኝ ስንዴ እፍኝ የማትሞላ ስንቅ እየቋጠረችላቸው እንዲዋጉ አስገድዷቸዋል።

አምና ቃላቸውን ከሰጡ አብዛኛዎቹ ምርኮኞች ያረጋገጥነው ከቤተሰብ አንድ ሰው በጦርነቱ ካልተሳተፈ የእርዳታ ስንዴ የማይሰጠው መሆኑን ነው። አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በእርዳታ የሚያገኘውን ስንዴ እንደ አሞሌ ጨው እያላሰ ሰዎችን ወደ ራሱ ለማቅረብ ስለሚጠቀምበት በአካባቢው የምግብ እህል እንዲመረት ፍላጎት እንደሌለው አንዱ ማሳያ ነው። በመሆኑም ይህንን እኩይ ተግባር ለማስቆም ከመንግሥት ጎን መቆም ከሁሉም ሰላምና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ ይሆናል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የሰኔ ወርና የጥፋት ተግዳሮቶቹ!

**ሙሉቀን ታደገ**

የሰኔ ወር እንደ አሁኑ የበጀት መዝጊያ ከመሆኑ አስቀድሞ አባቶቻችን እና እናቶቻችን ወሩ ምን አዲስ ነገር ያመጣልን ወይም ያመጣብን ይሆን ብለው በማሰብ “ምን ያመጣ ሰኔ ?” እያሉ ሲተርቱ ይሰማል። በተለይ ሰኔ እና ሰኞ ከገጠሙ ደግሞ ዘንድሮ በአገራችን ከፍተኛ ችግር ሊመጣ እንደሚችል በእርግጠኝነት ሲናገሩ ይስተዋላሉ።

በነገራችን ላይ ሰኔ እና ሰኞ ገጥመው ኢትዮጵያ አንድም ጊዜ ሰላም ሆና አታውቅም።የኢትዮጵያን ታሪክ በደንብ አገላብጠው ያልተመለከቱ አንድ አንድ ሰዎች ግን የሰኔ እና ሰኞ መግጠምን ችግር ያመጣል የሚለውን ፍራቻ አባቶቻችን እንዲሁ የሚሉት አፈ-ታሪክ አድርገው ይቆጥሩታል።ለጉዳዩ የኢትዮጵያን ታሪክ አገላብጦ ማየት ተገቢ ይመስለኛል ።

አሁን አሁን ግን ሰኔ እና ሰኞ ባይገጥሙም እንኳን በወርሐ ሰኔ በራሱ ኢትዮጵያ በመከራ ማዕበሎች እንድትናጥ የተፈረደባት መስሎ እየታየ ነው።በዚህ ወር ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን ፈጽሞ ሊረሷቸው የማይችሏቸው በርካታ አስከፊ የመከራ ማዕበሎች ተፈራርቀዋል። ይህን ስል በርካታ አመክንዮችን በማቅረብ እንጂ እንዲሁ በግብዝነት በመሆኑ በርካታ ማስረጃዎችን በማቅረብ አሳያለሁ።

የሰኔ ወር በመጣ ቁጥር ኢትዮጵያ አያሌ መከራዎች በላይዋ ላይ እየፈሰሱ አላስቆም አላስቀምጥ ሲሏት ተመለክተናል። ይህ ማለት ግን የሰኔ ወር ለኢትዮጵያ ምን መልካም ነገር አስገኝቶላት አያውቅም ማለት አይደለም።ነገር ግን የሰኔ ወር በመጣ ቁጥር ኢትዮጵያ በርካታ መከራዎች በላይዋ ላይ እንደ አሸን እየፈላ እንደአገር ለመቀጠል ስትቸገር ተመልክተናል።

ከጥንት ጅምሮ የሰኔ ወር በኢትዮጵያ ላይ ይዟቸው የመጣቸውን መከራዎች በታሪክ ተመልክቼ ሁሉንም ማቅረብ ባልችልም እንኳ የተወሰኑትን በወፍ በረር ላስቃኛችሁ ወደድኩ።

አንደኛ … የሰኔ ወር እና የኢትዮጲያ ሃዘን … ጀግናው ዘርዓይ ደረስ በአገረ ጣሊያን ለሞት ያበቃው በሰኔ ወር በተፈጠረ አንድ ክስተት ነበር። መቼም ሁሉም ሰው አንድ አይሆንምና ዘርዓይ ደረስ ደግሞ ማን ነው? የሚል አይጠፉ ይሆናል።ስለሆነም ስለጀግናው ዘርዓይ ደረስ ትንሽ ልበላችሁ።

ጀግናው ዘርዓይ ደረስ በኤርትራ ክፍለ አገር ሀማሴን አውራጃ ውስጥ አዝጋ በምትባል መንደር በ1908 ዓ.ም ተወለደ።ኢትዮጵያ በጣሊያን ፋሽስት ነፃነቷ ተደፍሮ በነበረበት ወቅት በወርሐ ግንቦት በ1937 ዓ.ም እ.አ.አ በኢጣሊያ ዋና ከተማ ሮማ ለአስተርጓሚነት ለመስራት ሄደ። ዘርዓይ ደረስ ወደ ኢጣሊያን ለማቅናት ምክንያት የሆነው ደግሞ ብዙ ኢትዮጵያውያን በእስረኝነት ወደ ኢጣሊያ ተወስደው ስለታሰሩና ታሳሪዎቹ ደግሞ ጣሊያንኛ ስለማይችሉ እነሱን በአስተርጓሚነት ለመርዳት ነበር። ዘርዓይ ደረስ ትግሪኛ፣ አማርኛ እና ኢጣሊያ ቋንቋዎችን አቀላጥፎ የሚናገር ምርጥ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ነበር።

በዶጋሊ ጦርነት ያለቁትን 500 ገደማ ኢጣሊያውያን ለማሰብ ኢጣሊያውያን ሰኔ 7 ቀን 1938 ዓ.ም በሮም ፒያሳ አደባባይ ተሰባሰቡ። ዘርዓይ ደረስም ወደ አደባባዩ እንዲመጣ ጥሪ ተደርጎለት ስለነበር ወደ ግብዣው ቦታ መጣ።

ወጣቱ ዘርዓይ ደረስም ወደ አደባባዩ በመጣ ጊዜ ራስ አሉላን አባ ነጋ በ1871 ዓ.ም በዶጋሊ ጦርነት ጀብዱ የፈፀሙበትን ጎራዴ ወገቡ ላይ ታጥቆ ነበር።በሮም ፒያሳ አደባባይ ጣሊያኖች በዶጋሊ ያለቁባቸው ወገኖቻቸውን ለማሰብ በወጡ ጊዜ በዶጋሊው ጦርነት ወገኖቻቸው ለወሬ ነጋሪ እንኳን ሳይተርፉ እንደ አገዳ የታጨዱበትን የእራስ አሉላ አባ ነጋን ጎራዴ መያዝ ምን የሚሉት ድፍረት ነው? ዘርዓይ ግን አድርጎታል።

ይህ በእንዲህ እያለ የኢጣሊያ ወታደሮች በሁለተኛው ዙር ወረራ ከአገራችን ኢትዮጲያ ሰርቀው የወሰዱትን የይሁዳ አንበሳ ሐውልት በሮም አደባባይ ሲዘባበቱበት ተመለከተ።በዚህም አላበቁ የኢትዮጵያዊያን ኩራት የሆነውን አረንጓዴ፣ ቢጫ ቀዩን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን ከመሬት ጥለው እየረገጡ ሲሳለቁበት አየ።በዚህም ክፉኛ በገነ! አንዳች ነገር ሰውነቱን ወረረው! ዘርዓይ ራሱን መቆጣጠር አቃተው።ንዴት በተቀላቀለበት ኢትዮጵያዊ ወኔና አልደፈር ባይነት ግርማ በወገቡ የያዘው ጎራዴ ከሰገቡ አወጣው። አውጥቶትም አልቀረ በአገሩ ሰንደቅ ዓላማ የሚቀልዱትን እና በሞአ አንበሳው ሐውልት የሚሳለቁ ጣሊያኖችን ለ50 ዓመታት በሚያውቁት ጎራዴ አናጋራቸው ! እንደ ገብስ ነዶ ወቃቸው።

ለክብረ በዓሉ የተሰባሰቡ ጣሊያኖችም የዘርዓይን እሳት የሚተፉ እጆች በተመለከቱ ጊዜ ብርክ ያዛቸው።የቻሉት እሮጠው አመለጡ። ያልቻሉት ደግሞ በራስ አሉላ ጎራዴ በዘርዓይ ክንድ ዳግም ተወቁ። በመጨረሻም ጣሊያኖችም ይህን ጀግና ተረባርበው ያዙት።አሰሩትም። ለህልፈት ተዳረገ።ይህ የሆነው በወርሐ ሰኔ ነው። ለዚህ ጀግና ኢትዮጵያዊ የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ የጦር መርከብ በስሙ እንዲሰየምለት ተደርጓል።

ሌላው የሰኔ ወር የኢትዮጵያን መከራ የሚጠራ ወር መሆኑን ለማሳያ በሁለተኝነት ያቀረብኩት ታሪክ በዘመነ ኃይለስላሴ የተፈጠረ አንድ ኩነት በወፍ በረር በመዳሰስ ነው። በዘመነ ኃይለስላሴ ኢጣሊያ ለሁለተኛ ጊዜ ኢትዮጵያን በወረራ ለመያዝ ባደረገችው ጦርነት በኢትዮጵያውያን ላይ በአለም የተከለከለውን የመርዝ ጋዝ ለጦርነት ተጠቅማ በርካታ ኢትዮጵያውያንን በአሰቃቂ ሁኔታ ገደለች።ይህን ተከትሎ ንጉሱ ወደ ጄኔቭ ሄደው በኢትዮጵያ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ግፍ በሚያስረዱ ጊዜ ጣሊያን የፈጸመቻውን ግፍ እንደጥሩ ነገር የቆጠሩ ጽንፈኛ ነጮች በኢትዮጵያውያን የሰቆቃ ጩኸት ጨፈሩ፤ ተዝናኑበትም። ኢትዮጵያውንም ለአምስት ዓመታት በችግር እየተወገሩ እንዲያልፉ ተፈረደባቸው።ይህ ግፍ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመው በፈረንጆች አቆጣጠር 1936 ወርሐ ሰኔ ነበር ።

የሰኔ ወር በኢትዮጵያ ጥፋት ጠሪ ወር እንድለው ያስገደደኝ ሌላው የታሪክ ገጠመኝ ደግሞ በሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም የተደረገው መፈንቅለ መንግስት ነው።ይህ መፈንቅለ መንግስት መካሄዱ እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ እና በኢትየጵያውያን ላይ መከራን በመከራ እየደራረበ ወደፊት መራመድ እንዳይችሉ ያደረገ ክስተት ይመስለኛል። ይህን ስል በኢትዮጵያ ንጉሳዊ ስርዓት መቀጠል ነበረበት ለማለት አይደለም።ፈጽሞ እንዲሆንም አልመኘውም። ነገር ግን በወጉ ያልተደራጁ እና የኢትዮጵያን የወደ ፊት እጣ ፈንታ መወሰን የማይችሉ በማርክሲሳዊ እና ሌኒናዊ ንድፈ ሃሳብ ብቻ አብደው ራሳቸውን እንደ አዋቂ የቆጠሩ ቁሞ ቀሮች የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ በደንብ ሳያገናዝቡ በእውር ድንብር አብዮት አመጣን በሚል ተደጋጋሚ የሞኝ ዘፈን ራሳቸውን እያታለሉ ኢትዮጵያን ወደ ጥፋት ገደል ለመጣል እና ወደ ገደሉ መሳብ አንድ ብለው የጀመሩበት በዚች ዕለት አድርጌ እቆጥረዋለሁ።

እንደሌሎች አገራት ህዝባቸውን ከጭቆና እና ከባርነት ያላቀቀ መፈንቅለ መንግስት ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያውያን አብዮቱ ፈነዳ የተባለበትን ቀን እንደ ብሄራዊ ቀን እንደሚያከብሩት ለአፍታም አያጠራጥርም።ነገር ግን አብዮቱ ከመጣ በኋላ አብዮቱን የሚመሩት ሰዎች አገሪቱን ለመምራት በራሳቸው አጀንዳ አፍላቂ መሆን ሲገባቸው ከሌሎች አገራት አጀንዳ እየተቀበሉ ከኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት ተጻራሪ ህግጋትን እና መመሪያዎችን በማውጣት እና እራሳቸውን ብቻ የለውጥ ሐዋርያ አድርገው በመቁጠር ተፎካካሪ ሃይሎችን ደግሞ ጸረ ለውጥ በማስመሰል ያሳስራሉ፤ ይገድላሉ፤ ያሳድዳሉ።ይህ አካሄድ ደግሞ ኢትዮጵያን ከአብዮቱ ጀምሮ ጦርነት እንዳይለያት ያደረገ ዐብይ ምክንያት ሆኖ እናገኘዋለን።ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም የኢትዮጵያ ጥቁር ቀን መጀመሪያ ስለመሆኑ አብዮቱን በሁለት ስንኝ እንዲህ ስል ለመግለጽ ተገድጃለሁ…

**አብዮት አመጣን ብለው የተኩራሩ፣**
**ስንዴን ለወፍ ጥለው እንክርዳድን ዘሩ ።**

ከላይ ከተጠቀሱት ኩነቶች በተጨማሪ የሰኔ ወር ይዞ የሚመጣቸው ጦሶች ኢትዮጵያን ለዘመናት ቀፍድዶ መላወሻ የሚያሳጣ ችግር ስለመሆኑ ሌላው ማሳያው ደግሞ በቅርቡ ሰኔ 24 እስከ ሰኔ 28 ቀን 1983 ዓ.ም በአገራችን የተፈጠረው ነገር ነው።በእነዚህ ቀናቶች የሽብር ቡድኑ ሕወሓት በሚያሽከረክረው ኢህአዴግ እና መሰል ተላላኪዎቹ የሽግግር መንግስት ለማቋቋም የጥፋት ጥንስስ መጠንሰስ የጀመሩበት ጊዜ ነው።ይህ ማለት በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያን በዘር የከፋፋለ ስርዓት ተዘርግቶ አሁን ኢትዮጵያ ለገባችበት ሰቅጣጭ የዘር በሽታ የዳረገን የሽግግር መንግስት ምስረታ የተከናወነበት ወቅት ነበር።

ከዚህ በተጨማሪም በእነኝህ ቀናቶች የሽብር ቡድኑ ሕወሓት ራስ የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት በእነዚህ ቀናቶች ነው። በሽብር ቡድኑ ራስ የተወሰኑ በርካታ ውሳኔዎች እስከዛሬ ድረስ ኢትዮጵያን አላራምድ ያሉ ችግሮችን ተፈጥረዋል።ሌላው የሰኔ ወር መከራ ጠሪ ወር መሆኑን ማሳያው ደግሞ በወርሃ ግንቦት 1997 ዓ.ም የተካሄደውን ምርጫ ተከትሎ በአዲስ አበባ የተፈጠረው አለመግባባት በጉልህ ተጠቃሽ ነው።የምርጫ ሄደቱን ተከትሎ በአጋጠመ ችግር ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ የሰላም መደፍረስ ተከሰተ።በዚህም የበርካታ ንጹሃን ወገኖቻችን ደም በከንቱ የፈሰሰ። በርካቶችንም ያለ ጧሪ ቀባሪም አስቀረ፡፡

በሰኔ ወር ከተፈጸሙና ኢትዮጵያን ጥቁር ማቅ ካለበሱ ከስተቶች ደግሞ አንዱ ሰኔ 16 ቀን 2011 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ለመግደል የተደረገው ሙከራ ነው።በዚች ቀን አሸባሪው ሕወሓት እና የጥፋት አሽከሮቹ በጎነጎኖት የክፋት ጉንግን ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለመግደል እረጅም ርቀት ሄደዋል።

ከናይሮቢ እስከ አዲስ አባባ በተዘረጋው የጥፋት ተልእኮ አገርና ህዝብ ዋጋ ከፍሏል። አሸባሪ ሀይሎቹ በመስቀል አደባባይም በመገኘት ጠቅላይ ሚኒስትሩን በመግደል በአገሪቱ ሁከት እና አለመረጋጋት በመፍጠር ለውጡን ለማደናቀፍ ሞክረዋል።

ቦምብ በመወርወር የሄዱበት የጥፋት መንገድ አገርና ህዝብን ሊያስከፍል የሚችለው ዋጋ የከፋ እንደነበር ለመገመት አይከብድም። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ደጋፊዎች ከጥፋት ሃይሎች ጋር ግብግብ ገጥመውና ከፍ ያለ ዋጋ ከፍለው ሴራውን መቀልበስ ችለዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለመደገፍ የወጡ ንጹሃን በጨካኞች ሴራ ለሞትና ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል። በዚች ዕለት የደም ጥመኞች በንጹሀን ደም የደም ጥማታቸውን ተወጥተዋል።ኢትዮጵያም ጥቁር ማቅ ለብሳለች።

ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ደግሞ ኢትዮጵያን ከአሸባሪው ሕወሓት መራሹ ኢህአዴግ የጥፋት መንጋጋ ፈልቅቀው ያወጡ የአማራ ክልል ጉምቱ ፖለቲከኞች እና ለውጥ ዘዋሪ ልጆች በጥፋት ሃይሎች በግፍ የተገደሉበት ቀን ነበር።እነኝህ ለውጥ ዘዋሪዎች ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን ብዙ ተስፋ ጥለውባቸው ነበር።ነገር ግን የፖለቲካ ሴራ ከሰኔ ወር አመጣሹ የጥፋት ልክፍት ጋር ተባብረው ባመጡት የጥፋት እሳት በሚዘገንን አኳኋን ተበሉ። ለውጡን በተፈለገው ልክ ያስቀጥላሉ የተባሉ ወንድሞቻችን ለአገራቸው ያለሙት ህልም መሬት ላይ አውርደው ሳይተገብሩ ከእነ ህልማቸው ላይመለሱ ወደማይቀረው አለም ሊሸኙ ግድ ሆነ።

ሰኔ 21 ቀን 2012 ዓ.ም ደግሞ ሌላ የጥፋት ድግስ በኢትዮጵያ ተከስቶ ነበር።በዚህች ቀን አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ በጨካኞች ተገደለ።ከአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ሞት ጋር በተያያዘ በበርካታ የአገሪቱ ክፍሎች በተለይም በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሁከት ተፈጠረ።

እንደሚታወቀው ሰኔ 21 ቀን 2012 ዓ.ም ከራሳቸው የፖለቲካ ጥቅም ውጭ ለኢትዮጵያ ለአንድ ጊዜም እንኳን ተጨንቀው የማያውቁ የራስ ወዳድነት ልክፍት በሽታ የተጠናወታቸው የፖለቲካ ቁማርተኞች በአርቲስቱ ሞት የተሰማንን ሃዘን ለማዘን ሳይፈቅዱልን ቀሩ።በርካቶች እንዲገደሉ፤ ለዘመናት ያፈሩት ሃብት ንብረታቸው እንዲወድም፣ ከመኖሪያ ቀያቸው በጎሳቸው ተመርጠው እንዲፈናቀሉ ተደረገ።አንዳንድ ከተሞች ሙሉ በሙሉ ወደሙ። በሃዘን ላይ ሌላ ልብን የሚያቆስል ሃዘን አከናነቡን።በዚህች ቀን በግብዞች ግብታዊ እርምጃ በርካታ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ንብረቶቻቸው ሙሉ በሙሉ እንዲዘረፉ እና እንዲቃጠሉ ተደረገ።በሰኔ ወር አይለፍልሽ የተባለች የምትመስለው ኢትዮጵያም እጅጉን ተከፋች።በጥቁር ደም ተለወሰች ።

አሸባሪው ሕወሓት ዳግም ወረራ የፈጸመበትን እና በሰሜኑ አገሪቱ ክፍል ከፍተኛ ግፍ እንዲፈጽም በር የከፈተውን ወረራ የጀመረው በወርሐ ሰኔ 2013 ዓ.ም ነው። በዚህ ወረራ አሸባሪው ሕወሓት ህዝባዊ ማዕበል በመፍጠር ከመቀሌ እስከ ጣርማ በር፣ ከአበርገሌ እስከ ደብረታቦር፣ ከማይጠብሪ እስከ ጭና የደረሰ ውጊያ አደረገ።በዚህም በርካታ ኢትዮጵያውያን መስዋዕት ሆኑ።በርካታ የመንግስት እና የግል ድርጅቶች ወደሙ።ከዚህ ወረራ ጋር ተያይዞ በእስከዛሬዋ ቀን ድረስ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ዋጋ እየከፈለች ትገኛለች።

የዘንድሮው ሰኔ ደግሞ ምን ያመጣ ይሆንተብሎ ሲፈራ … «የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል» እንዲሉ በጋምቤላ ክልል የተጀመረው ጸረ ኢትዮጵያ ጉዞ ወደ ወለጋ ተሸጋግሮ የአለምን ህዝብ ከጫፍ እስከጫፍ ያሳዘነ እና ያስቆጣ ተግባር ተፈጸመ።በርካታ ንጹሃን በግፍ ተገደሉ።ይህ የግፍ ጭፍጨፋ ኢትዮጵያ ብቻ አይደለም የአለምን ህዝብ አስለቀሰ።ዛሬም እያስለቀሰ ነው። በተለይም ከለውጡ ማግስት የተሞከሩ ሴራዎች በታሰበው መንገድ ተሳክተው ቢሆን አገራዊ ፈተናዎችን የቱን ያህል ሊሆን እንደሚችል ማሰብ አይከብድም። ለዚህም ታሪካዊ ጠላቶቻችንና የነሱ ተላላኪ የሆኑ ባንዳዎችን ማሰብ ተገቢ ነው። አገሬ ከሰኔ ወር መግባት ጋር ተያይዞ ከሚፈጠሩ የጥፋት ማዕበሎች ፈጣሪ አብዝቶ እንዲጠብቅሽ ምኞቴ ነው።ሰላም !!

**ከናይሮቢ እስከ አዲስ አበባ በተዘረጋው የጥፋት ተልእኮ አገርና ህዝብ ዋጋ ከፍሏል። አሸባሪ ሀይሉቹ በመስቀል አደባባይም በመገኘት ጠቅላይ ሚኒስትሩን በመግደል በአገሪቱ ሁከት እና አለመረጋጋት በመፍጠር ለውጡን ለማደናቀፍ ሞክረዋል።**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## አዩቴ ኢትዮጵያ የግብርና ቴክኖሎጂ ውድድር - አሸናፊ ወጣቶች

**ዳግም ከበደ**




በፈጠራ ሥራ የሚሰማሩ ወጣቶችን መደገፍ አገር የምትሻውን ጠንካራ አቅምና እድገት ለማምጣት ወሳኝ እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። አዳዲስ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች የኑሮ ዘይቤን ከማሻሻል ባሻገር ጊዜን፣ ገንዘብንና ጉልበትን በተገቢው መንገድ ለማስተዳደር ይረዳል። ለዚህ ነው መንግሥታት ፖሊሲዎቻቸውን ሲቀርጹና ረዘም ያሉ የእድገትና ምጣኔ ሀብት አስተዳደር እቅድ ሲነድፉ ብሩህ አእምሮ ያላቸው የፈጠራ ባለሙያዎችን የሚደግፉበትን መንገድ በቀዳሚነት የሚያመቻቹት።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በልዩ ልዩ ዘርፎች ላይ አጋዥ ሚና ያላቸው የቴክኖሎጂ፣ የዲጂታል እንዲሁም የተለያዩ ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶችን የሚያግዙ የፈጠራ ሥራዎች ላይ የሚሰማሩ ግለሰቦችን በልዩ ሁኔታ የማበረታታትና የመደገፍ ፖሊሲዎች እየተከተለ እንደሆነ የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ። በዋናነትም ታዳጊዎች ክህሎታቸውን አዳብረው እምቅ አቅማቸውን ለአገር ልማት እንዲያውሉ በትምህርትና ማሰልጠኛ ተቋማት ለማገዝ እየተሰራ መሆኑንም መረጃዎች ያሳያሉ። ይህ እርምጃ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን በመሰብሰብ፣ በማብቃት፣ ወደ ውጤት በመቀየርና የሥራ ዕድል በመፍጠር ኢትዮጵያ ያላትን ብዙ የወጣት ኃይል ሀብት መጠቀም የምትችልበትን ሥርዓት ይፈጥራል።

ከዚህ ባሻገር የግል ተቋማት፣ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ ያሉና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ አካላት ልዩ ልዩ ዘርፎች በቴክኖሎጂና አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦች ታግዘው የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ በፕሮግራማቸው ድጋፍ ሲያደርጉ ይስተዋላል። በተለይ ወጣቶች የፈጠራ አቅማቸውን እንዲጠቀሙና ሃሳቦቻቸውን እውን እንዲያደርጉ ለማገዝ በግል ተቋማት አማካኝነት የሚቀረጹ ፕሮጀክቶች አሉ።

የዝግጅት ክፍላችንም በዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ አምድ ላይ መንግሥት ዘርፉ እንዲያድግና የፈጠራ ባለሙያዎች አቅማቸውን ተጠቅመው ውጤታማ ሥራ እንዲሰሩ ከሚያደርገው ድጋፍ ባሻገር የሌሎች አካላት ድርሻ ምን ይመስላል? የሚለውን ሃሳብ ለመዳሰስ እንሞክራለን። በተለይ በቅርቡ የግብርናውን ዘርፍ በቴክኖሎጂ ለማገዝ የሚረዳ የፈጠራ ውድድር ስላዘጋጀው ሄይፈር ኢትዮጵያ "አዩቴ ኢትዮጵያ ቻሌንጅ" እና ውድድሩን ተካፍለው በስኬት ስላጠናቀቁ ወጣቶች የሚከተሉትን ጉዳዮች እናነሳለን።

ማህደር አካሉ በሄይፈር ኤንድ ሰስቴነብል ኢትዮጵያ የአዩቴ ኢትዮጵያ ቻሌንጅ መሪ አዘጋጅ ነች። ሄይፌር ኢትዮጵያ ስላዘጋጀው የግብርና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ውድድር፣ እውቅና መስጠትና ሽልማትን በተመለከተ ላነሳንላት ጥያቄዎች በሚከተለው መልኩ ምላሽ ሰጥታናለች።

ስለ ሄይፈር ኢንተርናሽናል ተልእኮ ስትናገር "ምድርን እየተንከባከቡ ረሃብን እና ድህነትን ማጥፋት ነው" በማለት ላለፉት 75 ዓመታት ኑሮ ለከበደባቸው ማሕበረሰቦች የከብት እርባታ እና የዘላቂ ግብርና ሥልጠና እና ድጋፍ ሲሰጥ የቆየ ተቋም እንደሆነ ትናገራለች። በአሁኑ ጊዜ ዩናይትድ ስቴትስን ጨምሮ በ21 አገሮች የሚገኙ የአገር ውስጥ ምግብ አምራቾች ንግዶቻቸውን እንዲያስፋፉ እና ለመኖር የሚያስችል በቂ ገቢ እንዲያገኙ ለማገዝ እየሰራ መሆኑንም ትገልፃለች።

እንደ መሪ አዘጋጇ ማህደር ገለፃ በ2021 ሄይፈር ከመላው አፍሪካ ለተውጣጡ እጅግ ተስፋ የሚጣልባቸው የግብርና ቴክኖሎጂ ኢኖቬተር ወጣቶች የገንዘብ ስጦታ የሚሰጠውን አዩቴ አፍሪካ ቻሌንጅ በይፋ አስጀምሯል። የአዩቴ አፍሪካ ቻሌንጅ በአህጉሪቱ ካሉት ታላላቅ የግብርና ውድድሮች አንዱ ለመሆን ያለመ ሲሆን፤ ይህም የአፍሪካ ወጣቶችን ኃይል ከተለያዩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋር በማጣመር በመላ አፍሪካ የሚገኙ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች ምርታቸውን እና ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ የማድረግ ርእይ ያለው ነው። ይህንን ለማሳካትም፣ ሄይፈር በያዝነው ዓመትም በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የፈጠራ ውድድሮችን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማዘጋጀት አቅዶ፣ የመጀመሪያውን ሀገራዊ የግብርና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ውድድሩን ለኢትዮጵያውያን ወጣቶች "አዩቴ ኢትዮጵያ ቻሌንጅ" በሚል ስያሜ በኢትዮጵያ አካሂዷል።

ሄይፈር ኤንድ ሰስተነብል ኢትዮጵያ ከበርካታ የመንግሥት አካላት እና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ውድድሩን መርቶታል ያለችው ማህደር አካሉ፤ አዩቴ ኢትዮጵያ ቻሌንጅ የአህጉር አቀፉ የአዩቴ አፍሪካ ቻሌንጅ ሀገር አቀፍ መልክ መሆኑን ትገልፃለች። የአዩቴ ኢትዮጵያ ቻሌንጅ ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አነስተኛ አርሶ አደሮችን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ እና ምርትና ምርታማነትን፣ ገቢን፣ የፋይናንስ አቅርቦትን የመቋቋም አቅምን መፍጠር የሚችሉ የግብርና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሃሳቦችን መርጦ መሸለም ነው። አዩቴ ኢትዮጵያ ቻሌንጅ በመላው ኢትዮጵያ ከሚገኙ ወጣት አመልካቾች ልቀው ለሚወጡ ወጣት የአግሪ-ቴክ ፈጠራ ባለሙያዎች በሙሉ ክፍት እንደነበርም ታስረዳለች።

### የመጨረሻው ቀንና የውደድሩ አሸናፊዎች

የሄይፈር ፕሮጀክት ኢንተርናሽናል አዩቴ ቻሌንጅ የመጨረሻ የአመልካቾች ውድድር በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ነበር የተካሄደው። በቴክኖሎጂ ውጤት አዲስ የፈጠራ ሃሳብ ውድድሩ ተመዝግበው ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ለመጨረሻው አምስት እጩ ተወዳዳሪነት የተመረጡት ወጣቶችም በስፍራው ተገኝተው ሃሳባቸውንና የሰሩትን ሥራ ለዳኞች፣ ለተጋባዥ እንግዶች ማቅረብ ችለዋል።

ፕሮጀክቶቻቸውን ባቀረቡበትና የመጨረሻ አሸናፊ ይፋ በሆነበት እለት በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በአውቶሞቲቭ ኢንጂነሪንግ የዲግሪ ተመራቂ የሆነችው መስከረም የማነ አንደኛ በመውጣት 10 ሺህ ዶላር አሸናፊ ሆናለች። ወጣቷ የፈጠራ ባለሙያ መስከረም ለገበሬው በተለይ ደግሞ የዶሮ እርባታ ላይ ተሰማርተው ለሚሰሩ አርሶ አደሮች ሽታን የሚቀንስና ምቹ የሆነ "የዶሮ ማርቢያ ቤት" በመስራትና በማስተዋወቅ ነው ተሸላሚ መሆን የቻለችው።

መሪ የፕሮግራሙ አዘጋጅ የሆነችው ማህደር አካሉ ለዝግጅት ክፍላችን ባደረሰችን መረጃ መሰረት የዶሮ ማርቢያው ለአሶአደሩ ኑሮ መሻሻል፣ ዘመናዊ የማርቢያ ዘዴ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ተብሎ ስለታሰበበት በዳኞች ተመርጦ ለአሸናፊነት መብቃቱን ነግራናለች። እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ዶሮ የማርባትና ለገበያ የማቅረብ አቅም ቢኖርም በዘመናዊ መንገድ በብዛትና ጥራት የሚሰራው ሥራ ግን አነስተኛ እንደሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ለዚህ እንደ አንድ ችግር ተደርጎ የሚወሰደው ደግሞ ቴክኖሎጂን መሰረት አድርጎ የመስራት ተግዳሮት በመኖሩ ነው። ይህንን መሰል ችግር ለመቅረፍ ደግሞ ሄይፌርን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ዘርፉን ለማበረታታት እየሰሩ ይገኛሉ።

ሌላኛው "የአዩቴ ቻሌንጅ" የግብርና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሥራ ተወዳዳሪ በመሆን ከአምስቱ የመጨረሻ እጩዎች ወስጥ ውድድሩን በሁለተኝነት ያጠናቀቀው ይስሃቅ አምደስላሴ ነው። ወጣቱ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ከወሎ ዩኒቨርሲቲና በማኔጅመንት ከዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ምሩቅ ሲሆን፣ በአዩቴ የግብርና ቴክኖሎጂ ውድድር ላይ የሰራው ፈጠራ የግብርና መረጃዎችን በቀላሉ ለተጠቃሚዎች የሚያደርስ መተግበሪያ "ኢንተራክቲቭ አፕሊኬሽን" (AgrInfoBot) ነው። አብዛኛውን ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ከመረጃ መዛባትና ትክክለኛነት አንፃር ምርትና ምርታማነትን ጨምሮ በርካታ ኪሳራዎች እንደሚደርሱ ይታወቃል። የዚህ ወጣትና የቴክኖሎጂ ፈጠራ ባለሙያም ይህንን ለማስቀረት ያግዛል ያለውን መተግበሪያ በመስራቱ ምክንያት የአዘጋጆቹንና የዳኞቹን ቀልብ በመሳብ የሁለተኛ ደረጃን በመያዝ የ6 ሺ 500 የአሜሪካን ዶላር ተሸላሚ መሆን ችሏል።

በአዩቴ የግብርና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሥራ ላይ በመጨረሻ አምስት እጩነት ከቀረቡት ውስጥ የሦስተኛ ደረጃን ይዘው ያጠናቀቁት ደግሞ ሳሙኤል ጌታቸውና ዮሴፍ ላቀው ናቸው። በአዲስ አበባ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ (አስቱ) የኤሌክትሪካል ኮምፒዩተር ኢንጅነሪንግ እንዲሁም የሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ ተማሪ የሆኑት ሁለቱ የፈጠራ ባለሙያዎች "ከመህር በፊትና በኋላ" የግብርና የባለሙያ ምክር አርሶ አደሩ የሚያገኝበትን ዲጂታል መተግበሪያ መስራት ችለዋል። ይህ ቴክኖሎጂ ተግባር ላይ ሲውል በቂ የባለሙያ ምክር የሚገኝበትን አማራጭ የሚፈጥር መሆኑ በዳኞች ታምኖበት በሦስተኛ የአሸናፊነት ደረጃ ላይ ሊቀመጥ ችሏል። በዚህም 3ሺ 500 የአሜሪካ ዶላር አሸናፊ በመሆን ከአዘጋጆቹ የእውቅና ሽልማት ተቀብለዋል።

### የእስቱ መልእክት

በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል በተካሄደው የመጨረሻ ዙር ውድድር ላይ በርካታ እንግዶች ተገኝተው ነበር። ከእነዚህ መካከል የሥራና ክህሎት ሚኒስትቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን ይገኙበታል። በመልእክታቸውም "ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ሄይፌርን የመሳሰሉ የግብርና ቴክኖሎጂን ለማላቅ ለሚሰሩ ወጣቶች የሚያደርጉትን ድጋፍ ያበረታታል" ከማለታቸውም ባሻገር በውድድሩ ላይ ተካፋይ ሆነው ላሸነፉት የፈጠራ ባለሙያዎች እንኳን ደስ አላችሁ የሚል መልእክት አስተላልፈዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ንጉሱ አፅንኦት ሰጥተው ከተናገሩት መካከል በቅርቡ የገጠር ሥራ አጥነት ዋነኛው ነበር። በአስደንጋጭ ፍጥነት እያደገ መሆኑን አንስተው ግብርናው በበቂ መልኩ ሥራ መፍጠር አለመቻሉን ገልጸዋል። የአየር ንብረት ለውጥን ጨምሮ፣ በረሃማነት እና ከፊል ደረቃማ አካባቢዎች ውስጥ ያለው ጨዋማነት፣ ከፍተኛ ዝናብ በሚዘንብባቸው አካባቢዎች አሲድነት፣ ተባዮች እና በዝናብ ጥገኝነት ምክንያት በርካታ ችግሮች እንደሚከሰቱም አንስተዋል። ይህንን ችግር ለመቋቋም መሰል የቴክኖሎጂ ፈጠራ ባለሙያዎችን ማበረታታት እንደሚያስፈልግም አንስተው መንግሥት በቂ ድጋፍ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

አዴሱዋ ኢፍዲ በሄይፈር ፕሮጀክት ኢንተርናሽናል፣ የአፍሪካ ከፍተኛ ምክትል ፕሬዚዳንት ናቸው። በውድድሩ መክፈቻ ላይ በተመሳሳይ እንደተናገሩት በኢትዮጵያ ሰፊ ምርት ሊሰጥ የሚችል መሬት፣ የሰው ሃይል እንዳለ ገልጸዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ለቴክኖሎጂ ቅርብ የሆኑና አዳዲስ የፈጠራ ሃሳብ ላይ መስራት የሚችሉ ወጣቶች በብዛት እንዳሉ በመግለጽም ይህን ማቀናጀትና መስራት ከተቻለ እራስን ከመመገብ አልፎ ለቀሪው ዓለም የሚተርፍ የግብርና አቅም መፍጠር እንደሚቻል ተናግረዋል። ሄይፌር ኢንተርናሽናልም ይህን ለመደገፍ መሰል ፕተሮጀክቶችን በመቅረጽ እንደሚሰራ ቃል ገብተዋል።

### ስለ አዩቴ ኢትዮጵያ

ሄይፈር በጣም ተስፋ ለተጣለባቸው ወጣቶች የግብርና ቴክኖሎጂ (አግሪቴክ) ፈጣሪዎች የገንዘብ ድጎማዎችን ይሸልማል። ይህን እሚያደርገው በአፍሪካ በሚያካሂደው ዓመታዊው አዩቴ "AYuTe Africa Challenge" በኩል ነው። ይህ የውድድርና ሽልማት ፕሮጀክት በየዓመቱ እስከ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ ነው። በኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ናይጄሪያ፣ ሀገር አቀፍ ውድድሮች ሩዋንዳ፣ ሴኔጋል እና ኡጋንዳ በ2022 በእያንዳንዱ ሀገር እስከ 20 ሺህ ዶላር ይሸለማሉ። አዩቴ ኢትዮጵያ ቻሌንጅ፣ የግብርና ቴክኖሎጂ (አግሪ-ቴክ) ፈጠራ ውድድር ለኢትዮጵያውያን ወጣቶች የተዘጋጀ ሲሆን በሄይፈር ፕሮጄክት ኢንተርናሽናል ተነሳሽነት በግንቦት 23 ቀን 2022 በይፋ የተጀመረው ነው። ብቃት ያላቸው ወጣት የፈጠራ ባለሙያዎችንና ጀማሪዎችን የመለየት እና የመሸለም ዓላማ ከመያዙም በላይ አነስተኛ ገበሬዎችን ለመርዳት አዲስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለውጥ የሚያመጣ አስተዋፅዖ በማድረግ እና በኢትዮጵያ የግብርናውን ዘርፍ ማሻሻልን ታሳቢ ያደረገ ነው። ውድድሩ ከ 18 እስከ 29 ዓመት እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ እና ለሁሉም ወጣት ኢትዮጵያውያን ክፍት ነበር።

በስምንት ቀናት ውስጥ በጠቅላላው 535 ማመልከቻዎች ቀርበው ነበር። ከአጠቃላይ አመልካቾች 56 ሴት እና 479 ወንድ ነበሩ። በተጨማሪም 108 አመልካቾች የዩኒቨርሲቲ ወይም የኮሌጅ ተማሪዎች ሲሆኑ፣ 228 አመልካቾች ደግሞ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ናቸው። 59 አመልካቾች የማስተርስ ዲግሪ የያዙ ሲሆን 56 ደግሞ 12ኛ እና ከዚያ በታች የትምህርት ደረጃ ያላቸው ነበሩ። ይህም በኢትዮጵያ ወጣቶች ለፈጠራ ሃሳብ እና ክህሎት የሚሰጡት ትኩረት እጅግ አበረታች መሆኑን የሚያመላክት ነው። ፕሮጀክቱ ለእነዚህ የፈጠራ ባለሙያዎች ተስፋ ሰጪና በቀጣይ በተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂ ላይ አዳዲስ ሃሳብ እንዲያመጡ በር ከፋች መሆኑ ተመስክሮለታል።

## ወቅታዊ ትንታኔ

# የአገር ሕልውናን በሁለት እግር አቁሞ ለማስቀጠል

ምሕረት ሞገስ

የአገር ህልውና በዋናነት ከአገረ መንግስት ጋር የሚተሳሰር ሲሆን፤ በሥሩ የመንግስት ድንበር ማስጠበቅን ጨምሮ የአገር ሰላም እና መረጋጋት እንዲሁም የኢኮኖሚ ዕድገትን ይመለከታል።ነጋድራስ ባይከዳኝ በ1909 ዓ.ም በታተመው ‹‹የመንግስት እና የሕዝብ አስተዳደር›› በተሰኘው መፅሃፋቸው ‹‹ኢትዮጵያ ራሷን በኢኮኖሚ ካልቻለች ነፃ አገር ናት ማለት አይቻልም›› ሲሉ አስፍረዋል።ይህንን ያሉት ከ100 ዓመት በፊት ቢሆንም፤ አንዳንዶች አሁንም ድረስ ያልዳበረ ኢኮኖሚ እና ያልተረጋጋ የዲሞክራሲ ስርዓት በመኖሩ የኢትዮጵያ ህልውና ተጠብቋል፤ ሉዋላዊነቷ ተከብሯል ለማለት አያስደፍርም ሲሉ ይደመጣሉ፡፡

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ህልውናዋን አስጠብቃ እንደአገር ቆማ ሶስት ሺህ ዓመታትን ያስቆጠረች፤ ሕዝቡም እርስ በእርስ የተጋመደ ወደፊትም የማይነጣጠል መሆኑ ይገለፃል።በተቃራኒው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ ሌሎች ምሁራንና ፖለቲከኞች ጥንቃቄ ካልተደረገ አገሪቷ ለመበተን በቋፍ ላይ ስለመሆኗ ይናገራሉ።

በአዲስ ወግ የውይይት መድረክ ላይ በጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት ኃላፊ ሚኒስትሩ ዶክተር ቢቂላ ሁሬሳ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ህልውናዋ አደጋ ላይ ወድቋል።አጣብቂኝ ውስጥ ገብታም ኢትዮጵያውያን አድነዋታል።አባቶች የኢትዮጵያን ሕልውና ለማስጠበቅ ዕልህ አስጨራሽ ትግል አካሒደው ሕይወታቸውን ሰውተው አሁን ላለችበት ደረጃ አድርሰዋታል፡፡

አሁን ደግሞ የውስጥ እና የውጪ ጠላቶች አስበውበት ኢትዮጵያን ለማዳከም ከፍተኛ ፕሮጀክት ቀርፀዋል።ፕሮጀክቱን የቀረፁት ገንዘብ መድበው፣ የሰው ኃይል እና ሌሎች በቂ ዝግጅቶች አድርገው በስፋት እየሰሩበት መሆኑ ግልጽ ነው፤ በመሆኑም መላው ኢትዮጵያውያን ይህንን ተረድተው ከመንግስት ጎን በመሆን በጥንቃቄ የአገርን ሕልውና ማስቀጠል እንደሚኖርባቸው ይመክራሉ።

የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጅጌ በበኩላቸው እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ ፖለቲካ የፅንፈኝነት ሰለባ ሆኗል።ያለመደማመጥ ጫፍ ለጫፍ ቆሞ መጓተት፤ የአፈሙዝ እና የአፈና አስተሳሰብ ለዘመናት ተንሠራፍቶ ቆይቷል።ይህም የአገር ሕልውናን አደጋ ላይ ጥሏል።ይህንን ችግር ለማለፍ በማህበራዊ፣ በፖለቲካው፣ በፀጥታ እና በደህንነት ጉዳይ ላይ አሁንም ትልልቅ ሥራዎች መሠራት አለባቸው።ነገር ግን ከምንም በላይ ገመድ መጓተቱ ቀርቶ በውይይት በማመን፤ የሃሳብ ሽግግር ማምጣት ይገባል ይላሉ።

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍሰሃ ይታገሱ፤ ፅንፍ የሆኑ አቋሞችን ለማቀራረብ ውይይት እና ክርክር በመጨረሻም በወሳኝ ጉዳዮች ላይ መግባባት ይገባል ይላሉ።አገር በሶስት ምሶሶዎች ላይ መቆም አለባት።የመጀመሪያው ነፃ ብቃት ያላቸው ተቋማት መኖራቸው ወሳኙ ነው።

የሲቪል ሰርቪስ፣ የዴሞክራሲ ተቋማትም ሆኑ የአገር ደህንነት እና የፀጥታ ተቋማት ጠንካራ መሆን እንደሚጠበቅባቸው አመልክተው፤ በመንግስት እና በሕዝብ መካከል ያለ ስምምነት እና መተማመንም የአገር ህልውናን ለማስቀጠል ወሳኝ ስለመሆኑ ያብራራሉ።

ተቋማት በተገቢው መልኩ አልተገነቡም። በተጨማሪ በታሪክ፣ በሰንደቅ ዓላማ እና በሌሎችም ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ አገራዊ መግባባት የለም።የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታውም ላለፉት ሃምሳ አመታት ቢጀመርም ተመልሶ ወደ ኋላ እየተቀለበሰ አገሪቷ በርካታ ችግሮች ሲገጥሟት ቆይቷል።ለዚህ መፍትሔው መወያየት እና መግባባት የአገር ህልውና ዘላቂነትን ለማረጋገጥ በቀጣይ ትውልድ ላይ መሥራት ይገባል።በውይይት የሚያምን እርስ በእርስ እንደወንድም የሚተያይ፣ የሚዋደድ፣ የሚከባበር እና የሚደጋገፍ ሕዝብ እንዲኖር ከትምህርት ቤት ጀምሮ መሠራት አለበት።

ዴሞክራሲን ለማስፈን አገርን ለማስከበር፣ የአገርን አንድነት ለማስጠበቅ፤ አገርን ከብተና ለመታደግ ብሔራዊ አቅሞች ወሳኝ ናቸው።ብሔራዊ አቅም ሲባል የመጀመሪያው ዲፕሎማሲ ሲሆን ሌላኛው ኢንፎርሜሽን ነው።እንዲሁም ወሳኝ የሆነው ደግሞ ኢኮኖሚው፣ ፀጥታ እና ደሕንነት መሆናቸው ይነገራል።እነዚህ በተገቢው መልኩ መገንባት ብቻ ሳይሆን መጋመድ እና መሬት ላይ መውረድ አለባቸው።

በተለይ ለፀጥታ እና ደህንነት ልዩ ትኩረት መሰጠት አለበት ሲባል፤ መከላከያ የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችን ተዋፅኦ የተረጋገጠበት መሆን እንዳለበት በሕገመንግስቱ አንቀፅ 38 ተቀምጧል።ይህ ብቻ አይደለም፤ መከላከያ በብቃት፣ በጥራት፣ ተወዳዳሪ እና ትውልድ ተሻጋሪ መሆን አለበት።አቅሙ ጦርነት ውስጥም ሆነ ፀጥታን ማስከበር ተግባር ላይ ከመሰማራቱ ቀድሞ የሚፈራበት ደረጃ ላይ መድረስ አለበት።ለዚህ ደግሞ የፀጥታ እና ደህንነት ተቋሙ በተገቢው መልኩ ተዋፅኦን ማዕከል አድርጎ መገንባት እንዳለበት ይገለፃል።ተዋፅኦ መኖር አለበት ሲባል ከብቃት ጋር እንጂ፤ እንዲሁ ለተሳትፎ ብቻ ማካተት ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝንም ይገለፃል።ብቃትን መሰረት አድርጎ የሚኖር ተዋፅኦ በየአካባቢው ለሚኖር ግዳጅ አፈፃፀም ትልቅ ጉልበት ከመሆኑም በተጨማሪ፤ ከሕዝብ ጋር ያለው ግንኙነት ጠንካራ እና ሕዝቡ ማንኛውም ፀጥታ አስከባሪም ሆነ መከላከያን የኔ ነው ብሎ እንዲያምን ያደርጋል።

ከፀጥታ እና ደህንነት በተጨማሪ በዋናነት የአገር ህልውናን ለማስቀጠል ወሳኙ ጠንካራ ኢኮኖሚን መገንባት እንደሆነ የሚናገሩት ደግሞ የፕላን እና ልማት ሚኒስትሯ ዶክተር ፍፁም አሰፋ ናቸው።እንደ ዶክተር ፍፁም ገለፃ፤ ኢኮኖሚው ሲነሳ አሁን የዓለም ተፅዕኖ ቀላል አይደለም የዕዳ ጫና እና የሥራ አጥነት ችግሮች በፖሊሲዎች ማሻሻል አስፈላጊ ነው።ፖሊሲዎችን ማሻሻል ማህበራዊ ፍትሕን ለማረጋገጥ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እና የማክሮ ኢኮኖሚ ማረጋጋት ወሳኝ መሆኑን ያስረዳሉ።

የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የሥርዓተ ፆታ እኩልነት፣ ድህነት ተኮር ዕርዳታ መስጠት አገርን በማረጋጋት በኩል ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱ በመጠቆም፤ በኢኮኖሚው ላይ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት እንደተጀማመረው በግብርና ላይ ኢንቨስት ማድረግ እና መሠረተ ልማት በማስፋፋት እኩል ተደራሽነት እና ፍትሃዊነትን ሲረጋገጥ የአገር ሕልውና ጥያቄ ውስጥ የሚገባበት አጋጣሚ እንደማይፈጠር ያመለክታሉ።

የግል ዘርፉ የአጭር ጊዜ ጥቅም ሳይሆን ረዥም ጊዜን ማዕከል አድርጎ አስተማማኝ ሥራዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል ካሉ በኋላ ጊዜያዊ ግንባታዎች እና አጫጭር ስራዎች ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ አምራች ኢንዱስትሪው ግብርና ላይ ትኩረት ማድረግ ለአገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ስለመሆኑ ያብራራሉ።

ኢኮኖሚውን ማሳደግ እየተፈጠረ እና እየታየ ካለው የውጪ ተፅዕኖ ለመላቀቅ ወሳኝ መሆኑን በማመልከት ለአገር ሕልውና ኢኮኖሚው ላይ አተኩሮ መስራት አማራጭ የማይቀመጥለት ጉዳይ ስለመሆኑም ይናገራሉ።

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕልኸኛ ነው ፅናት እና ወኔም ያለው ህዝብ ነው። በመሆኑም ይህንን ወኔውን ወደ ሥራ በማምጣት ጠንካራ ኢኮኖሚ እንዲገነባ ማድረግ ይገባል። ነገር ግን ይህንን ማድረግ ካልተቻለ፤ አገርን ከውጪ እርዳታ እና ብድር ተላቃ በሁለት እግሯ እንድትራመድ ማስቻል አዳጋች ይሆናል።እንዲሁም እልሁን በግጭት ማስተንፈስ ላይ ትኩረት ከተደረገ ውጤቱ በተቃራኒው ይሆናል።ነፍስ እየጠፋ አገር እየወደመ የኢትዮጵያን ህልውና ማፅናት አዳጋች ይሆናል።**

በቀድሞ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ በዛብህ ገብረየሱስ በበኩላቸው፤ ለአገር ህልውና ወሳኞቹ ተቋማት ናቸው።አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሰዎች፣ በአደረጃጀቶች እና በአሰራር ስርዓቶች ተሰናስለው በህግ ተመስርተው ለሕዝብ ካላገለገሉ የአገር ጉዳይ አሳሳቢ እንደሚሆን ያመለክታሉ።በሞያ እና ውል ባልተገባበት የፖለቲካ ፍላጎት መቀላቀል ሳቢያ፤ የመንግስት ሥራ እና ፖለቲካው መቀላቀሉ እንደትልቅ ችግር የሚታይ መሆኑን በማመልከት፤ የአገር እና የሕዝብ ጥቅም ተገቢውን ሥፍራ ሲያጣ ችግር ፈጥሮ አገርን ለአደጋ ሊያጋልጥ የሚችልበት ሁኔታ ስለመኖሩ ያስገነዝባሉ።

የመንግስት ሥራ የሚቋቋመው በህግ ነው።በሕግ ለህዝብ ተገቢ አገልግሎት ይሰጣል።ሕግ ሲተገበር መንግስት ብቻውን አድራጊ ፈጣሪ የሚሆንበት ሁኔታ ቀርቶ ተገልጋይ ሕዝብም የመገልገል መብቱ የሚከበርበት ዕድል ይኖራል።ለዚህ ሰብአዊ ልማት አስፈላጊ ነው።ፍትሃዊነት እና እኩልነት ለማስፈን፤ ህግ በእኩልነት ሁሉም ላይ እንዲተገበር እንዲሁም ማንም ሆነ ማን በህግ ተገቢውን አገልግሎት ያልሰጠ እና ውጤት ያላመጣ ተጠያቂ እንዲሆን ምቹ ሕግ ማውጣትና ያንንም ማስተግበር ሲቻል፤ የአገር ህልውና ማረጋገጥ አዳጋች እንደማይሆን ያመለክታሉ።

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር አቶ እንዳለ ንጉሴ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ የአገር ህልውናን ለማረጋገጥ በሕግ መመራት ያስፈልጋል።ጠንካራ ተቋምም ሆነ ኢኮኖሚ መሰረቱ ህግ ነው።የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ሕገ መንግስት ማሻሻል የሚገባም ከሆነ አሻሽሎ እንደየጋራ የቃልኪዳን ሰነድ በመውሰድ በዛ ላይ ተመስርቶ ተቋማትም ሆነ ኢኮኖሚው እንዲሁም ዲፕሎማሲው የሚመራበትን መንገድ መፍጠር ይቻላል።የጋራ በግልፅ የሚታወቅ ሕግ ሳይቀመጥ ተቋማትም ሆነ ዲፕሎማሲው ላይ ትልልቅ ስራዎችን ማከናወን እና መቆጣጠር አዳጋች ስለመሆኑም አመልክተዋል።

ብዙዎች እንደሚያነሱት የሚሰሩት ሥራዎች ውይይት እና መግባባት ላይ መመስረት አለባቸው፤ ተቋማትን ለማስተካከል ብዙ ሥራዎች ቢከናወኑም ሥራው ቀጣይነት እንዲኖረው በጠንካራ የሕግ መሰረት ላይ መመስረት አለበት።እኩል ተጠቃሚነት፣ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው የመኖር ነፃነት፣ ዘላቂ ሰላም እና ዕድገት ለማምጣት ግልፅ አሰራር እና ሕግ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕልኸኛ ነው። ፅናት እና ወኔም ያለው ህዝብ ነው። በመሆኑም ይህንን ወኔውን ወደ ሥራ በማምጣት ጠንካራ ኢኮኖሚ እንዲገነባ ማድረግ ይገባል። ነገር ግን ይህንን ማድረግ ካልተቻለ፤ አገርን ከውጪ እርዳታ እና ብድር ተላቃ በሁለት እግሯ እንድትራመድ ማስቻል አዳጋች ይሆናል።እንዲሁም እልሁን በግጭት ማስተንፈስ ላይ ትኩረት ከተደረገ ውጤቱ በተቃራኒው ይሆናል።ነፍስ እየጠፋ አገር እየወደመ የኢትዮጵያን ህልውና ማፅናት አዳጋች ይሆናል።

አገርን እያነደደ ስላለው የጉያ ረመጥ ተቆጭቶ ለልማት መነሳሳት የግድ ነው።ነገር ግን መነሳሳት ጥፋትን በጥፋት ለመመለስ፣ ለበቀልና ነፍስ ለማጥፋት ሳይሆን አገር በመገንባት፤ ህግ ማክበርና ማስከበር ላይ በመትጋት ነው።ምንም እንኳ በዋናነት ህግ ማስከበር የመንግስት ኃላፊነት ቢሆንም፤ የአገር ሕልውና እንዲረጋገጥ በየአካባቢው፤ እያንዳንዱ ግለሰብ ለህግ መከበር ሚናውን መወጣት አለበት።ዜጎች ለኢኮኖሚ ዕድገት የተቻለውን ሚና በመወጣት እና ጠንካራ ሥራ በመስራት የአገርን ህልውና ማስቀጠል ያስፈልጋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ለአገር ተረካቢ ሕፃናት፤ ለነፍሰ ጡርና አጥቢ እናቶች ጥሪ ምላሽ የሰጠ ተግባር

ሰላማዊት ውቤ

ቦታው ቦሌ ክፍለ ከተማ ነው። በቅርቡ ተገኝተን እንዳስተዋልነው በክፍለ ከተማው ሁለት ወረዳዎች በሚገኙ ፋና እና ንስር ሸማች ማህበራት አልሚ ምግቦች ክፍፍል ተካሂዷል። ብዙ ነፍሰ ጡር እናቶች፤ አጥቢ (እመጫት) እናቶች በመርሐ ግብሩ ታድመዋል። ዕድሜያቸው ከወር ጀምሮ እስከ ሦስት ዓመት የሚገመት ሕፃናትን ያቀፉና ያዘሉም ይገኙበታል። ከእናቶቹ አንዳንዶቹ ፈዘዝ ያሉ ይመስላሉ። ያቀፉና ያዘሏቸው ሕፃናት የፋፉ አይደሉም። ቀጫጭንና መጠናቸው ትንንሽ ነው ። ክብደታቸው ቀላል ለመሆኑ በእቅፍና እዝላቸው ውስጥ ጎልተው አለመታየታቸው ይመሰክራል። ከታቀፉትና ከታዘሉት ሦስት ዓመት የሞላቸው ሕፃናት ከሌላው ሰውነታቸው ይልቅ ሆዳቸው ጎልቶ ይታያል። የእጅና የእግር አጠቃላይ አካላቸው ከሲታ ነው። ሰውነታቸው የጫጫ ይመስላል። እንደአዋቂዎቹ የፊት ገጽታዎች ፈዝዘዋል። ንቁና ደስተኛ አይመስሉም።

ሁኔታቸው ከሦስት አሥርት ዓመታት በላይ ወደ ኋላ ተጉዤ ስለተመጣጠነ ምግብ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ ሳለሁ የተማርኩትን አስታወሰኝ። በተለይ ተመጣጣኝ ምግብ እጥረት ያለበት ሰው በከፍተኛ ሁኔታ የሰውነት ክብደቱ እንደሚቀንስ ፤ ኃይል እንደሚያጣ ፤ ገጽታው ላይ መፍዘዝ የሚታይበት የመሆኑ ምልዕክት መጣልኝ።

ወይዘሮ ዘቢደሩ በላይ እንደነገሩን የያዟት ሕፃን ሦስት ዓመት ሆኗታል። ፊቷ ድንቡሽ ያለ ነው። አስተያየቷ ፍዝ ይመስላል። ምክንያቱም ዓይኗ ለረጅም ጊዜ ዕይታ ውስጥ ቢሆንም ትኩረቷ ምንም ዓይነት ነገር ላይ እንዳላረፈ በግልፅ ይስተዋላል። ወይዘሮዋን ከዚህ በፊት አልሚ ምግቦችን መገበዋት ያውቁ እንደሆን ጠየቅኳቸው። እሳቸውም ዓይናቸውን ካተኮሩበት ሳያነሱ ከየት መጥቶ ለእንጀራ በሽሮውም በሆነልኝ ሲሉ ነበር የመለሱልኝ ። እንደመልሳቸው ሕፃኗ ብዙም ጤና የላት። በቅርቡ ሆስፒታል ወስደዋት ፕሮቲን እጥረት አለባት ተብላለች። በቦታው የተገኙት በወረዳው በደሃ ደሃ ተመልምለው አልሚ ምግብ ውስዱ ተብለው በመሆኑ እጥረቱን ይተካላታል ብለው ተስፋ ያደርጋሉ።

ወይዘሮ ዓለምፀሐይ በዳዳ የፊት ገጽታዋ ሲስተዋል ሃሳብ የገባው ይመስላል። እንዳወጋችን በቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 3 ነዋሪ ነች። ያዘለችውን የአንድ ዓመት ልጅ ጨምሮ ሦስት ሕፃናት ልጆች አሏት። ቀደም ሲል የቤተሰብ ምጣኔ ግንዛቤ ያላት ባለመሆኑ በዓመት ልዩነት ነው የወለደቻቸው። ሁለቱ ሆዳቸው ጎልቶ ቢታይም ሌላው ሰውነታቸው የመነመነ ሆኖ ይታያል። ሲጫወቱ በተደጋጋሚ ይወድቃሉ። ያለቅሱና ይነጫነጫሉም። ታናሻቸው ቢሆንም ታላቃቸው የሚመስለው ያዘለችው ሕፃን ነው። ተመጣጣኝ ምግብ ልትመግባቸው የሚያስችል ገቢ የላትም። የምትደዳደረው ቋሚም ባይሆን ባለቤቷ ያገኘውን ሰርቶ አልፎ አልፎ በሚሰጣት ገንዘብ ነው። ይሄ በሸማች ማሕበሩ እንደተሰጣት ያለውን የቆርቆሮ ወተት፣ ፓስታ፤ አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ አልሚ የሚባሉትን ምግቦች መሸመት ቀርቶ ለዕለት ዳቦ መግዣም አይበቃም ። ልጆቿ በአብዛኛው በእናት ጡት ወተት ቢያድጉም ከስድስት ወራቸው በኋላ በቂ ወይም ተጨማሪ የሚባለውን ምግብ አላገኙም። በመሆኑም በየጊዜው ይታመማሉ። ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት የአልሚና የተመጣጣኝ ምግቦች ድጋፍ ተሰጥቷት አታውቅም ። ድጋፉ ሲደረግላት የመጀመርያዋ ነው።

በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 ነዋሪ የሆነችው ወጣት መስከረም ወንድሙ ሌላዋ የድጋፉ ተጠቃሚ ናት። ከጉራጌ ዞን ዶቤ ከሚባል አካባቢ ነው የመጣችው። የግለሰብ ቤት ኪራይ



ወይዘሮ ዘቢደሩ በላይ



ወይዘሮ ዓለምፀሐይ በዳዳ



ወይዘሮ ሀና ደጉ



ወጣት መስከረም ወንድሙ

ውድ በመሆኑና አቅሜ ስለማይፈቅድ በጉልበቴ እያገለገልኩ ዘመድ ጋር ተጠግቼ ነው የምኖረው የምትለው መስከረም ቋሚ የምትለው ሥራ የላትም። ኑሮዋን ያገኘችውን በተለይም ሹሩባ እየሰራች ስትገፋ ነው የቆየችው። ልጅ ከወለደች በኋላ ግን ስላላመቻት አቁማዋለች። የዘጠኝ ወር ሕፃን ልጇንና ራሷን መመገብ የሚያስችላት የተለያዩ ተመጣጣኝና አልሚ ምግቦችን በነፃ አግኝታለች። ዘይትን ጨምሮ ዱቄት፣ የቆርቆሮ ወተት (ኒዶ ) ፣ ምስር ክክ፣ ማኮሮኒ እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬ ካገኘቻቸው ይጠቀሳሉ። የተመጣጠነና የአልሚ ምግብ ድጋፉን በዚህ ኑሮ ውድነት ማግኘት ለእሷ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ድጋፉ ክረምቱን ሙሉ ዘላቂ ነው መባሉ ተስፋዋን አለምልሞላታል። ድጋፉን ሳገኝ የመጀመሪያዬ ነው የምትለው መስከረም በነፍሰ ጡርነቷ ብታገኘው ሕፃን ልጇ የበለጠ ዕድገቱ የሰመረ ይሆን እንደነበር ለ15 ቀን በወሰደችው ከአመጋገብ ጋር የተያያዘ ስልጠና መገንዘቧንም ትናገራለች።

እናቶች ነፍሰ ጡር ሲሆኑ ለራሳቸው ከሚያስፈልጋቸው ምግብ በተጨማሪ ለፅንሱ ዕድገት ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ተመጣጣኝና አልሚ ምግቦችን መመገብ እንዳለባቸው ተገንዝባለች። ከስልጠናው እናት ሕፃኑን ከፀነሰችበት እስከ ውልደቱ ባሉት 270 ቀናት የአመጋገብ ሥርዓት ትኩረት ማድረግ እንደሚገባም መረዳቷን ታወሳለች።

ከሥልጠናው በፊት ግንዛቤ ባይኖረኝም ለልጄ እስከ ስድስት ወር ጡቴን አጥብቸዋለሁ። አሁንም እያጠባሁት ነው። በተጨማሪም ጡቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለት ዓመት እስኪሞላው ተጨማሪ ምግቦችን እየመገብኩት እገኛለሁ። ድጋፉ ልጄን በዘላቂነት እንድመግብ ይረዳኛል ብዬ አስባለሁ ብላናለች በቀጣይነቱ ላይም ተስፋ እንዳላት በማከል።

ራሴን አሞኛል። በጣም እያዞረኝ ነው ስትል ትክዝ፤ ፍዝዝ፤ ቅዝዝና ድክምክም እንዳለች ለጥቂትና አጭር ጥያቄዬ የሰለች በሚመስል ስሜት መልስ የሰጠችኝ ወይዘሮ ሀና ደጉ ነች። እንደመልሷ ድጋፉን ስትወድስ ያገኘኋት አንድ ዓመት ከሰባት ወር ዕድሜ ባለው ሕፃን ልጇ አማካኝነት ነው። ልጇ ተመጣጣኝና አልሚ ምግቦችን በማግኘቱ ዕድለኛ ነው ባይ ነች። በሕፃናት አስተዳደግና አመጋገብ ዙርያ ለ15 ቀን በተሰጣት ሥልጠና ዕድሉን ማግኘት የነበረበት ከስድስት ወር በኋላ መሆኑን በመረዳቷ ልጇ ተጨማሪ ምግብ ከሚያስፈልገው ወቅት ተላልፎ ቢሆንም አልሚ ምግቡ ደርሶለታል ትላለች። ያገኘችው ድጋፍ በእህል፣ በእንስሳት ተዋጽኦ፤ በአትክልትና ፍራፍሬ መበልፀጉን ታወሳለች። ስራ ስለሌላትና መግዣ ገንዘቡ ስላልነበራት ፤ የነዚህን



ዶክተር ሀና የሺንጉስ

ውህዶችና በንጥረ ነገሮች የበለፀገ ገንፎ ዱቄት አዘጋጅታ ባለመስጠቷ ከዚህ ቀደም የወለደችው የ10 ዓመት ልጇ የጓደኞቹን ያህል የትምህርት ፍላጎት የለውም። ትምህርት ቤት ቢሄድም ለትምህርቱ ትኩረት አይሰጥም ። አቀባበሉም ደከም ያለ እንደሆነ መምህራኖቹ እንደነገሯት ትገልፃለች። በአንዳንድ ነገሮች ንቁ እንዳልሆነም ታወሳለች። ዕድገቱና የሰውነቱ መጠንም በዕድሜው ልክ የሚጠበቀውን ያህል እንዳልሆነም ትጠቅሳለች። በሥልጠናው እንዲህ ዓይነቱ የጤና ችግር ሕፃናት ከጽንስ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመታቸው በቂና በንጥረ ነገሮች የበለፀጉ ምግቦች ባለማግኘታቸው የሚመጣ መቀንጨር የተሰኘው በሽታ እንደሆነ መገንዘብ ችላለች። ግንዛቤውን ማግኘቷ ልጇን በሚገባ ለመንከባከብ እንድትተጋ አድርጓታል።

የድጋፍ መርሐ ግብሩ በፋናና ንስር ሸማች ማሕበራት የተደረገ ሲሆን በተገኙሁበት ፋና ሸማቾች ማሕበር በክፍለ ከተማው ስድስት ወረዳዎች የሚገኙ አጥቢ ፤ ነፍሰ ጡርና ዕድሜያቸው እስከ ሶስት ዓመት የደረሰ ሕፃናት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡

ብዙዎቻችን ምግብ አመጋገብን ረሃብን ከማስታገስና ከመጥገብ ጋር እናያይዘዋለን። ሆኖም ዓላማው ይህ ብቻ ሳይሆን ገና ከጠዋቱ አእምሯዊና አካላዊን ጨምሮ ሁለንተናዊ የሰውነታችንን ግንባታ ማዕከል በማድረግ የተመጣጠነ መሆንም ይኖርበታል ሲሉ ስለድጋፉ ማብራሪያቸውን የጀመሩት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ሕፃናትና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሀና የሺንጉስ ናቸው።

ያልተመጣጠነ ምግብ ዕድገትን ያቀነጭራል። መቀንጨር የሚከሰተውም የሕፃናት ዕድሜና ቁመት ሳይመጣጠን ሲቀር ነው። በሽታው ከጽንስ ጀምሮ ሕፃናት ሁለት ዓመት እስኪሞላቸው የተመጣጠነ ምግብ ባለማግኘታቸው ከሥርዓተ ምግብ መዛባትና አለመመጣጠን ጋር ተያይዞ የሚመጣ ነው ብለዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ የወደፊት አገር ተረካቢ የሆኑትን ሕፃናትን ከዚህ የጤና ችግር መታደግ የሚያስችል የአልሚ ምግቦች ድጋፍ ውሱን ሆኖ መቆየቱንም አስታውሰዋል። የቀዳማይ ልጅነት ዕድገት ከእናት ጽንስ ጀምሮ እስከ ሁለትና ሦስት ዓመት ይዘልቃል። ሆኖም በዚህ ወቅት ነፍሰ ጡርና አጥቢ እናቶች እንዲሁም ሕፃናት የዓልሚ ምግቦች ተጠቃሚ ባለመሆናቸው ለተለያዩ በሽታዎች እየተጋለጡ እንዳሉም አክለዋል። አካል መቀጨጨንና ቁመት ማሳጠሩን አስታውሰው በአእምሮ ላይ የተለያዩ ጉዳቶችን የሚያደርስ መሆኑንም ለአብነት አንስተዋል። ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ የጤና ችግሩን ለማቃለል የከተማው አስተዳደር ከሌሎች ዘርፍ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሰራ መገኘቱንም አንስተዋል። በመርሐ ግብሩ ገቢያቸው ዝቅተኛ ለሆነና ገቢ ለሌላቸው በ11ዱ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ለሆኑ ለዘጠኝ ሺህ እናቶች የተደረገው የአልሚ ምግቦች ድጋፍ ማሳያ መሆኑንም ተናግረዋል።

ድጋፉ የተያዙትን ቀጣይ ሁለት የክረምት ወራቶች ጨምሮ በ2015 ዓ.ም ተጠናክሮ የሚቀጥልበት ሁኔታ ተመቻችቷልም ብለዋል።

ከጽንስ ጀምሮ በሚከሰት በሽታ በኢትዮጵያ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ለጉዳት መዳረጋቸውን ቆየት ያሉ ጥናቶች ያመለክታሉ። በፈረንጆቹ 2016 የተደረገን ጥናት ዋቢ አድርጎ ከጤና ሚኒስቴር የወጣ መረጃ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ 38 በመቶ ያህል የሕብረተሰብ ክፍሎች ለመቀንጨር በሽታ ተዳርገዋል። ነገር ግን በመከላከሉ ረገድ ኢትዮጵያ በሰራችው ባለ ዘርፈ ብዙ የተቀናጀ ሥራ በፈረንጆቹ 2017 ዓ.ም 20 በመቶ ያህሉን ችግር መቀነስ ችላለች። ችግሩን መቀነስ ካስቻላት ዋናውም ነፍሰ ጡር እናቶችና ዕድሜያቸው እስከ ሁለት ዓመት ላሉ ሕፃናት አልሚ ምግቦችን በስፋት በማቅረብ ነው።

ሕብረተሰቡ በተለይም ነፍሰ ጡር እናቶች ተመጣጣኝ ምግብ እንዲመገቡ የሚያስችል ግንዛቤ ፈጠራ ላይም በብርቱ ስትሰራ መቆየቷም መሆኑ ለውጤቱ መመዝገብ ላቅ ያለ ሚናን ተወጥቷል ። እንደ ጥናቱ በሽታው እናቶችንና ሕፃናትን ከመጉዳቱ ባሻገር በኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ላይም በየዓመቱ 16 ነጥብ 5 በመቶ የራሱ ተፅዕኖ ያሳድራል። በየዓመቱ 58 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር የሚያሳጣት በመሆኑ ለነፍሰ ጡርና አጥቢ እናቶች እንዲሁም ለሕፃናት እየተደረገ ያለው የዓልሚ ምግብ አቅርቦት ድጋፍ ተጠናክሮ ይቀጥል ።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን በ1958 ዓ.ም የታተሙ ጋዜጦችን ዓይተናል።የመረጥናቸው ዜናዎች በማኅበራዊ ጉዳዮች ማለትም በምግብ መጠጥና ትራንስፖርት ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው።እነዚህም በዚያ ዘመን በትራንስፖርቱ ረገድ ከታሪፍ ውጪ በማስከፈልና ትርፍ በመጫንና የሚታዩ ችግሮችን የሚያሳዩ ናቸው።ይህ ችግር አሁንም ድረስ በዘርፉ ከሚስተዋሉ ችግሮች አንዱ ሆኖ ይታያልና በዚያ ዘመን የነበረውን እውነታ ከአሁኑ ጋር ለማነፃፀር እንዲረዳ አቅርበነዋል።

### የአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡሶች ሥራቸውን አቋመው ዋሉ

በአዲስ አበባ የሚገኙ የአንበሳ የማመላላሻ አውቶቡስ አሠሪዎችና ሠራተኞች መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት ከትናንት በፊት የኩባንያው ሠራተኞች ሥራቸውን አቁመው ነበር።

የአንበሳ የማመላላሻ አውቶቡስ፤ በትናንትናው ቀን ለሕዝቡ የሚሰጠውን ግልጋሎት በማቋረጡ ምክንያት በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ታክሲዎች ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አደባባይ እስከ አራት ኪሎ፤ ከዚያም በቅርብ ለሚገመት ርቀት ላለው ሥፍራ ከመደበኛው ሃያ አምስት ሳንቲም የመጓጓዣ ክፍያ ዋጋ ወደ አንድ ብር ከፍ ሲያደርጉት፤ ሩቅ ናቸው ለተባሉ ሥፍራዎች ደግሞ የክፍያው ዋጋ ከብር በላይ ሆኖ ውሏል፡፡

በብዙ የሚቆጠር የአዲስ አበባ ኗሪ ሕዝብ ሠራተኛው፤ ተማሪውና እንዲሁም ነጋዴውም ወደ ተግባሩ ለመሠማራት፤ እንደቀድሞው አውቶቢሱን ሲጠባበቅ ቆይቶ፤ በከተማው ውስጥ የማይዘዋወር መሆኑን ከተረዳ በኋላ፤ የከተማው ታክሲ ነጂዎች የጠየቁትን መክፈል ግድ ሆኖበታል፡፡

በዚሁ በድንገት በተፈጸመ የሥራ ማቆም ምክንያት ኩባንያው በብዙ ሺህ የሚቆጠር የገቢ ኪሣራ የደረሰበት መሆኑ ታወቀ።በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት አስፈላጊውን ጥናት የሚደረግበት ቢሆንም፤ የአንበሳ የማመላለሻ አውቶቡሶች ሥራቸውን ከቀትር በኋላ ቀጥለዋል፡፡

በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ለማስወገድ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ርምጃ የወሰደ ሲሆን፤ የመቶ አለቃ ሚካኤል አመዴ በዚሁ ጉዳይ ላይ በሰጡት አጭር ማብራሪያ ‹‹ የሥራው ማቆም በድንገት የተፈጠረ ለመሆኑ ጉዳዩ በመጣራት ላይ ነው›› ብለዋል።

አንበሳ አውቶቡስ አሠሪና ሠራተኞች የኅብረት ሥራ ስምምነት የተፈራረሙት ኅዳር 1 ቀን መሆኑ ይታወሳል።

(ታኅሳስ 5 ቀን 1958 የወጣው አዲስ ዘመን)

### የመንጃ ፍቃድ የሌላቸውና ትርፍ የጫኑ ሹፌሮች ተቀጡ

### ከኢትዮጵያ ወሬ ምንጭ

ጅማ፤ በጅማ ከተማ ውስጥ ንጋቱ ወልደ ትንሳይ የተባለ ሹፌር ከተፈቀደለት ክብደት በላይ 14 ሰው አሳፍሮ፤ የግል ጥቅምን ብቻ በመሻት የተሳፋሪውን ሕዝብ መብት ሳይጠብቅ ባደረገው ጥፋት በጅማ አውራጃ ፖሊስ ትራፊክ አባሎች ተይዞ ቀርሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ጥፋቱ ስለተረጋገጠበት ፶ ብር መቀጫ ከፍሎ ለሁለት ወር መኪና እንዳይነዳ ተበይኖበታል፡፡

እንዲሁም ጌታቸው ተክለማርያም የተባለ ሹፌር ከተፈቀደለት ክብደት በላይ ፱ ሰዎች አሳፍሮ ሲጓዝ በትራፊክ ፖሊስ ተይዞ ጅማ ከተማ ሁለተኛ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ ፵፫ ብር መቀጫ እንዲከፍል ተፈርዶበታል፡፡

ከዚህም ሌላ ጀማል አህመድ የተባለ ሹፌር ከተፈቀደለት ክብደት በላይ ፫ ሰዎች አሳፍሮ ስለተገኘ በትራፊክ ፖሊስ ተይዞ በዚሁ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ፤ ጥፋቱ ስለተረጋገጠበት ፳፫ ብር መቀጫ እንዲከፍል የተፈረደበት መሆኑን በደረሰን ጽሁፍ ሊታወቅ ተችሏል።

* * *

ድሬዳዋ፤ በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ የትራንስፖርት ሕግ በመተላለፍ የመንጃ ፈቃድ ሳይዙና ከተወሰነላቸው ጭነት በላይ ትርፍ በመጫን ሲዘዋወሩ በመገኘታቸው በትራፊክ ፖሊሶች ተከታታይነት የተያዙት ፯ ሰዎች ወደ ወረዳው ፍርድ ቤት ቀርበው ፫፻፳ ብር መቀጣታቸውን የድሬዳዋ አውራጃ ግዛት ፖሊስ ጽ/ቤት በሰጠው ዜና ገልጧል፡፡

* * *

ሀገረሕይወት፤ ስሜነህ ተስፋዬ ፪ኛ ሽፈራው በቀለ የተባሉ የከባድ መኪና ሹፌሮች የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ ከተፈቀደላቸው በላይ እያንዳንዳቸው አሥር ሰዎች አሳፍረው በመገኘታቸው አንደኛው ፶ ብር ሲቀጣ ሁለተኛው ደግሞ ፴ ብር መቀጫ ከፍሏል።

(ኅዳር 28 ቀን 1958 የወጣው አዲስ ዘመን)

### የድሬዳዋ ዳቦ ጋጋሪዎች ስምምነት ፈረሙ

ከኢትዮጵያ ወሬ ምንጭ፡፡

ድሬዳዋ፤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ስለ ዋጋ መቆጣጠር ድሬዳዋ ከተማ በሚገኘው ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ኅዳር ፲፯ ቀን ስብሰባ ተደርጎ ነበር።የስብሰባውም ዓላማ በከተማው ውስጥ የሚገኙት ዘጠኝ ዳቦ ጋጋሪዎች የሚጋግሩት ዳቦ ኪሎ ግራም ከፍና ዝቅ በማለቱ የተነሳ ሲሆን፤ ዳቦ ጋጋሪዎች በስብሰባው ላይ ተገኝተው በአንድ ዓይነት ኪሎ ግራም እንዲጋግሩ አንድ ስምምነት ፈርመዋል፡፡

(ኅዳር 28 ቀን 1958 የወጣው አዲስ ዘመን)

### የመጠጥ ቤቶች ጉዳይ ለፓርላማ ቀረበ

### ከኢትዮጵያ ወሬ ምንጭ

የህግ መወሰኛ ምክር ቤት ስለ ሴተኛ አዳሪዎችና መጠጥ ቤቶች መስፋፋት ላይ ከተነጋገረ በኋላ፤ ጉዳዩን አግባብ ያለው የመወሰኛው ምክር ቤት ኮሚቴ ከሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ልዩ ኮሚቴ ጋር እንዲያጠና ትናንት ባደረገው ስብሰባ ወሰነ፡፡

በኢትዮጵያ የሴተኛ አዳሪዎችና እንዲሁም የመጠጥ ቤቶች መስፋፋት የሚያስከትለውን ፕሮብሌም ገልጸው፤ ምክር ቤቱ በጉዳዩ መክሮበት አንድ መፍትሔ እንዲገኝለት በማለት ለምክር ቤቱ ሐሳብ ያቀረቡት የተከበሩ አቶ አመዴ ለማ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ናቸው።

ይኸው ጉዳይ በቀደምትነት የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ከውጭ አገር ባስመጣቸው ኤክስፐርቶች በመጠናት ላይ መሆኑም ተገልጿል።

(ኅዳር 28 ቀን 1958 የወጣው አዲስ ዘመን)

# ዓለም አቀፍ

## ደቡብ አፍሪካ ውስጥ በአንድ የምሽት ክበብ ከ20 በላይ ወጣቶች ሞተው ተገኙ

ደቡብ አፍሪካ በአንድ የምሽት ክበብ ውስጥ ተሰብስበው ከነበሩ ወጣቶች መካከል ቢያንስ የ22 ወጣቶች ሕይወት አልፎ ተገኘ። የአገሪቱ ባለሥልጣናት ባልታወቀ ምክንያት ሕይወታቸው ያለፈውን ወጣቶች ሞት ምክንያት ለማወቅ ምርመራ እያደረጉ መሆናቸው ተገልጿል።

ወጣቶቹ ሞተው የተገኙት ቅዳሜ ሌሊት ለእሁድ አጥቢያ ሲሆን ዕድሜያቸውም ከ18 እስከ 20 የሚገመት እንደሆነ ባለሥልጣናት ተናግረዋል። ወጣቶቹ በባሕር ዳርቻዋ ትንሽ ከተማ ኢስት ለንደን ውስጥ በሚገኝ አንድ የምሽት ክበብ ውስጥ ወለል እና ጠረጴዛዎች ላይ እንዳሉ ሞተው ነው የተገኙት።

ከ22 የሚበልጡት ወጣቶች አስከሬንም ምናልባት ተመርዘው እንደሆነ ለማወቅ እንዲሁም ተጨማሪ ምርመራ ለማድረግ ወደተለያዩ የሕክምና ተቋማት ተወስደዋል። የደቡብ አፍሪካው ፕሬዚዳንት ሲሪል ራማፎሳ በወጣቶቹ ህልፈት የተሰማቸውን “ጥልቅ ሐዘን” ለሟቾቹ ቤተሰቦች ገልጸዋል።



“ይህ አሰቃቂ ሁኔታ የአገራችንን ወጣቶች አጠቃላይ ሁኔታን ለማሻሻል በሚረዱ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በምናደርግበት የወጣቶች ወር ላይ መከሰቱ በእጅጉ ያሳዝነናል” ሲሉ ፕሬዚዳንቱ በትዊተር ገጻቸው ላይ አስፍረዋል። የወጣቶቹ ሞት ያጋጠመበት የኢስት ኬፕ ግዛት አስተዳዳሪ የሆኑት ኦስካር ማቡያኔ፣ ለወጣቶቹ ህልፈት ምክንያቱ ምን እንደሆነ ሳይገልጹ “ከልክ ያለፈ የአልኮል መጠጥ አጠቃቀምን” በደፈናው አውግዘዋል።

ባለሥልጣኑ ወጣቶቹ ሕይወታቸው አልፎ በተገኘበት የምሽት ክበብ ተገኝተው “በማኅበረሰቡ መካከል ሆኖ እንደዚህ መጠጥ ሲሸጥ ወጣቶች ሊሞክሩት አይችሉም ብሎ ማሰብ አይቻልም” ብለዋል።አንድ የግዛቲቱ የሕዝብ ጤና ባለሥልጣን ለፈረንሳይ ዜና ወኪል (ኤኤፍፒ) እንደተናገሩት፣ ለወጣቶቹ ሞት መረጋገጥ ምክንያት እንዳልሆነ “በሰውነታቸው ላይ ምንም አይነት ቁስለት” አለመኖሩን በመጥቀስ ተናግረዋል።

“መርማሪዎች ናሙናዎችን በመውሰድ ምርመራ ካደረጉ በኋላ አንዳች ዓይነት መመረዝ በሰውነታቸው ውስጥ መኖሩን ያጣራሉ” ሲሉ ባለሥልጣኑ ተናግረዋል። በአንድ ምሽት ይህን ያህል ወጣቶች በአንድ ቦታ ተሰብስበው ለህልፈት መዳረጋቸው በደቡብ አፍሪካ ከፍተኛ ድንጋጤን መፍጠሩን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ልዑል ቻርለስ ”አንድ ሚሊዮን ዩሮ በሻንጣ መቀበላቸውን‘ አንድ ዘገባ ይፋ አደረገ

የዌልሱ ልዑል አንድ ሚሊዮን ዩሮ ከቀድሞው የኳታር ጠቅላይ ሚኒስትር በሻንጣ መቀበላቸውን ሰንደይ ታይምስ ዘገበ። እንደ ጋዜጣው ከሆነ ይህ ሻንጣ፣ በሼኽ ሐሚድ ቢን ጃሲም ከተሰጡት ሦስት ሻንጣዎች አንዱ ነው። አጠቃላይ ገንዘቡም ሦስት ሚሊዮን ዩሮ ይደርሳል ተብሏል።

የንጉሣዊያኑ ቤተሰብ ጽሕፈት ቤት በበኩሉ፣ ከሼኹ የተሰጡት ልገሳዎች በቀጥታ ወደ ልዑሉ የበጎ አድራጎት ሥራዎች መተላለፋቸውን ገልጿል። አካሄዱም ተገቢ ነበር ሲል ተካላክሏል። ክፍያው ሕገ ወጥ ስለመሆኑ ምንም የተገለጸ ነገር የለም። እንደ ሰንደይ ታይምስ ከሆነ፣ ልዑል ቻርለስ እአአ ከ2011 እስከ 2015 ባሉት ዓመታት ውስጥ ሦስት ጊዜ ገንዘቡን በአካል ተገኝተው ተቀብለዋል።

አንደኛው ክፍያ በክላረንስ ሃውስ (የዩናይትድ ኪንግደም ንጉሣዊያን ቤተሰብ መኖሪያ) መፈጸሙንም ዘግቧል። በሌላ ጊዜ ደግሞ በፎርትነም እና በማሰን በገንዘብ የሞሉ ሻንጣዎች መሰጠታቸውን ጋዜጣው አስነብቧል። ክላረንስ ሃውስ ባወጣው መግለጫ “ከሼኽ ሐሚድ ቢን ጃሲም የተሰጡ ልገሳዎች የልዑሉ የበጎ አድራጎት ሥራዎች ከሆኑት ወደ አንዱ በቀጥታ ተላልፏል። ትክክለኛውን አስተዳደራዊ ሂደትም ተከትሏል” ብሏል።

ገንዘቡን የተቀበለው የዌልስ ልዑል የበጎ አድራጎት ነው። ድርጅቱ “ሕይወትን መቀየር እና ዘላቂ ማኅበረሰብን መፍጠር” የሚል ዓላማ ያለው ነው። በአካባቢ ጥበቃ፣ ትምህርት፣ ጤና እና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ይሠራል።

ለጋሹ ሕጋዊ ነው ሲል ድርጅቱ ለሰንደይ ታይምስ ምላሽ ሰጥቷል። አዲተሮችም ክፍያውን አጽድቀውታል ሲል አክሏል። ለልዑል ቻርለስ የሚደረጉ ድጋፎች በቅርብ ጊዜያት ትችት እያስተናገዱ ይገኛሉ። ለአንድ



የሳዑዲ እርዳታ ሰጪ የዩኬ ዜግነት እና የክብር ሽልማት ለማስጠት ተሠርቷል በሚል ነው ትችቱ የተጀመረው።

ሜትሮፖሊታንት ፖሊስ ከልዑሉ የበጎ አድራጎት ድርጅት ጋር በተያያዘ ምርመራ በማድረግ ላይ መሆኑን በቅርቡ አስታውቋል። ድርጅቱ ለምርመራው ተገቢውን ትብብር በማድረግ ላይ እንደሆነ አስታውቋል። ክላረንስ ሃውስ በበኩሉ ልዑል ቻርለስ ከድጋፉ ጋር በተያዘ ስለተነሳው የዜግነት ጉዳይ እንደማያውቁ አስታውቋል።

የልዑሉ ድርጅት የቀድሞ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የነበሩት ማይክል ፋውሴት በዚሁ ዙሪያ ምርመራ መከናወኑን ተከትሎ ሥራቸውን ለቀዋል።“ከግብረ አበሮች” ጋር በመሆን ለቢሊየነሩ የንግድ ሰው ማሕፉዝ ማሪ ሙባራክ ቢን ማሕፉዝ የክብር ሽልማት ለማስጠት መንቀሳቀሳቸው በምርመራ ተረጋግጧል። የድርጅቱ የበላይ አካላት ጉዳዩን እንደሚያውቁ የሚያሳይ ምንም ማስረጃ የለም ሲል ድምዳሜውን እንዳስቀመጠ የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

# ስፖርት

# ሁስተኛው ‹‹ኬር ኦድ›› የሰላም ሩጫ

**ብርሃን ፈይሳ**




**በውድድሩ በርካታ የአትሌቲክስ ባለሙያዎችና ጥሪ የተደረገላቸው የመንግስት የስራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል፣**

ስፖርትና ሰላም የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው።ስፖርት ሰላምንና አብሮነትን እንዲገነባ ውድድሮች ትልቅ መድረክ ናቸው።ውድድሮችን ለማካሄድ ደግሞ ሰላማዊ አውድ ያስፈልጋል።ይህንን በገንዘብ የማይተመን የስፖርት ጥቅም ለህብረተሰቡ በማቅረብ ረገድ የተለያዩ ውድድሮች ይካሄዳሉ።ይህንን ታሳቢ በማድረግም የጉራጌ ዞን ዋና ከተማ በሆነችው ወልቂጤ የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር ተካሂዷል።መጠሪያውን ከቋንቋው የተዋሰውና ‹‹ኬር ኦድ›› የተሰኘው ይህ የጎዳና ላይ ውድድር ‹‹ለኢትዮጵያ ሰላም እንሩጥ›› በሚል መሪ ሃሳብ ታዋቂ አትሌቶችን ጨምሮ ከ20ሺ ያላነሱ የከተማዋን ነዋሪዎች በማሳተፍ ከትናንት በስቲያ ተካሂዷል።

በኢትዮጵያ ስፖርት በውጤታማነት ቀዳሚ በሆነው አትሌቲክስ በርካታ ውጤታማ አትሌቶችና አሰልጣኞችን ማፍራት ተችሏል።ይሁንና አገሪቷ በስፖርቱ እንዳላት አቅምና የተፈጥሮ ሁኔታ በሚገባት ልክ ተጠቃሚ ለመሆን አልቻለችም።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጥቂት የአትሌቲክስ ውድድር የሚያካሂዱ ድርጅቶች እንቅስቃሴ በመታየት ላይ ይገኛል።ከእነዚህ መካከል አንዱ የሆነው የኬር ኦድ የጎዳና ላይ ሩጫ ነው።የጉራጌ ዞን ያፈራቸው የአትሌቲክሱ ዓለም ከዋክብት የቀድሞ አትሌትና በዚህ ወቅት በግሎባል ስፖርት ማኔጅመንት የኢትዮጵያ ተወካይ ሆኖ በማሰልጠን ላይ የሚገኘው ተሰማ አብሽሮ፣ ወንድሙ አትሌት አየለ አብሽሮ፣ የኦሊምፒክ ቻምፒዮናውና የ10ሺ ሜትር ፈርጥ የሆነው ወጣቱ አትሌት ሰለሞን ባረጋ እንዲሁም ሌሎች በርካታ የስፖርቱ ባለሙያዎችና ወዳጆች የተመሰረተ ማህበር ነው።ባለፈው ዓመት የመጀመሪያ ውድድሩን ሲያካሂድ ዘንድሮም ለሁለተኛ ጊዜ በወልቂጤ ከተማ እጅግ ደማቅ በሆነ መልኩ አካሂዷል፡፡

በውድድሩም ላይ የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስተር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ የኢትዮጵያ አትሌትክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ፣ ምክትል ፕሬዚዳንቱ አትሌት ገዛኸኝ አበራ፣ የፌዴሬሽኑ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ቢኒያም ምሩጽ ይፍጠር፣ የጉራጌ ዞን አስተዳደር፣ የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት፣ ስመጥር አትሌቶችና አሰልጣኞች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው በርካታ እንግዶች ተገኝተዋል።

15 ኪሎ ሜትር በሸፈነው ውድድር ላይም በወንዶች ወጣቱ አትሌት ድንቃለም አየለ አሸናፊ ሆኗል።በአፍሪካ ቻምፒዮና 5ሺ ሜትር ውድድር 4ኛ ደረጃን በመያዝ የዲፕሎማ ባለቤት የነበረው አትሌቱ፤ የአየር ሁኔታውና ሩጫው የሚደረግበት ስፍራ ውድድሩን ፈታኝ እንዳደረገበት ተናግሯል።በሴቶች ደግሞ በ3ሺ ሜትር መሰናክል የኦሊምፒክ ብር ሜዳሊያ ባለቤት የነበረችው ጠንካራዋ አትሌት ሶፊያ አሰፋ በሴቶች ዘርፍ በቀዳሚነት ማጠናቀቅ ችላለች።አንጋፋዋ አትሌት መሰል የሃገር ውስጥ ውድድሮች መብዛታቸው ለአትሌቶችም ሆነ ለስፖርቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ጠቁማለች።

የኬር ኦድ ልማትና ስፖርት ማህበር ፕሬዚዳንት አሰልጣኝ ተሰማ አብሽሮ፤ ኬር ኦድ የሚለው ቃል በራሱ ፍቅርና አንድነትን የሚሰብክ መሆኑን ይገልጻል።የሩጫው ዓላማም ሰላምን መስበክ በመሆኑ ሁሉም በያለበት ይህንኑ ሃሳብ ማስተላለፍ እንደሚገባም አሳክቷል።የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ በበኩሏ ሰላምን ማዕከል በማድረግ ከመሮጥ ባለፈ ስለ ኢትዮጵያ ሰላም ሁሉም የሚገባውን ማድረግ እንዳለበት ጠቁማለች።

ሩጫው ያነገበው ዓላም ጥልቅ እና ትልቅ መሆኑን የገለጹት ደግሞ፤ የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት ናቸው።ይህ ወቅት ኢትዮጵያ በበርካታ የውጪና ውስጣዊ ችግሮች ውስጥ እያለፈች ያለችበት በመሆኑም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከሰላም ባለፈ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሌለ ተናግረዋል።በመሆኑም ከሩጫው ጎን ለጎን ለሰላም መረባረብ አስፈላጊ መሆኑን አሳስበዋል።

ውድድሩን ከአንድ እስከ ስድስት ባለው ደረጃ አጠናቀው መግባት የቻሉ አትሌቶ ከ75ሺ እስከ 5ሺ ብር የገንዘብ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።የዚህ ውድድር አካል የሆነና 10ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የሩጫ ውድድር በቅርቡ በቡታጅራ ከተማ የሚደረግ ሲሆን፤ በቀጣዩ ዓመት የሚካሄደው የወልቂጤ ሶስተኛው ዙር የ15 ኪሎ ሜትር ውድድር ጀምሮ ከተለመደው የሰኔ ወር ወደ ግንቦት ወር ተቀይሮ እንደሚደረግም ተጠቁማል፡፡

---


## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍ/ባለመብት እነ ማርቆስ ጌንቤሮ ጌቦ እና በፍ/ባለዕዳ አቶ ዳንኤል ጌንቤሮ ጌቦ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 67708 በ24/06/2012 ዓ.ም እና በመ/ቁ 78268 በ17/6/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በበጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤ.ቁ 224 የሆነ ቤት ጠቅላላ የቦታ ስፋት 1516 ቤቱ ያረፈበት ጠቅላላ በፕሮፖርሽን 195 ካ/ሜ ጠቅላላ በፕሮፖርሽን የሚደርሰው 330 ካ/ሜ ሲሆን ይዞታው ፕሮፖርሽን የሆነ የግራ ቀኙ አግድ ያለበት የሆነው የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 288,000(ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺ) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ነሐሴ 26 ቀን 2014 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ8፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት ¼ኛውን በባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬት የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዴሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍ/ባለመብት እነ ወ/ሮ ወይንሸት ሽፈራው እና በፍ/ባለዕዳ ወ/ሮ አሰራት ገ/ማርያም መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር/291306፤ 294859 12/12/2013ዓ/ም እና በ5/11/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 428 ካርታ ያለው የግቢው ስፋት 157 ካ/ሜ ቤቱ ያረፈበት 25 ካ/ሜ በፕሮፖርሽን ከግቢው ለቤቱ የሚደርሰው የቦታው ድርሻ ስፋት 10 ካ/ሜ ጠቅላላ በፕሮፖርሽን ለግለሰቡ የሚደርሰው የቦታው ስፋት 35 ካ/ሜ ከጠቅላላው ከግቢው መንግድ የሚነካው 66 ካ/ሜ ከቤት ቁጥር 428 መንገድ የሚነካው 14 ካ/ሜ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 29,980 (ሃያ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ብር) ሆኖ የትራዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ለነሐሴ 6 ቀን 2014 ዓ.ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ5፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3:30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን፤ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬት የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

## በደ-ብ/ብ/ክ/መንግሥት

ለአቶ አየለ ዜርቃሉ

ባሉበት

ከሳሽ MCC 17 ሚዛን ዲማ መንገድ ሥራ ድርጅት እና በተከሳሽ በአቶ አየለ ዜርቃሉ መካከል ስላለው የንብረት ጉዳት ካሳ ክስ ክርክር ጉዳይ ለ/4/11/2014 ዓ.ም 2፡30 ላይ ቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲቀርቡና መልስ እንዲሰጡ የማይቀርቡ ከሆነ በሌሉበት የሚወሰን መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በደቡብ/ምዕ/ኢት/ሕ/ክ/መንግስት የቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**

የባለንብረቱ ስም አህመድ መሀመድ የኑስ ሰሌዳ ቁጥር አማ-03-25818 የሻንሲው ቁጥር 5009620 ሞተር ቁጥር 2KD-7902266 ተሽከርካሪው አይነት አውቶብስ ሞዴል KDH202L- REMDYU ከላይ ደረጃው የተገለፀው የተሽከርካሪ ባለንብረት የኋላ ታርጋ ጠፋብኝ ብለው ከክልል ስለጠፋብኝ 25/08/2014 አመልክተዋል፡፡ ስለዚህ ሰሌዳው ወድቆም ተሰርቆም ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

**የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ቡድን**

ንብረትነቱ የኪንዶ ዲዳዬ ወረዳ አስተዳደር የሆነ የሠሌዳ ቁጥር ኮድ 4-24258 ኢ/ት የሞተር ቁጥር 1HZ-0857443 የሻንሲ ቁጥር JTEEB71J0070340377 የሆነ የመስክ ተሽከርካሪ ሰሌዳው/ታርጋ/ ጠፍቶብናል በማለት በቀን 29/09/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡

ስለዚህ ሠሌዳ ወድቆ ወይም ተሰርቆ ሌላ ሰው ሲጠቀም ያገኘ ሰው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሰባት ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እየጠየቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረበ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የጋሞ ዞን ትራንስፖርትና መንገድ ልማት መምሪያ**

ከሳሽ/አመልካች፡- ህብረት ኢንሹራንስ ኢ.ማ እና

በተከሳሽ/ተጠሪ፡- ፓስፊክ ኢንዱስትሪያል

መካከል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 1ኛ. ባንክ/ኢ. ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ በተከሳሽ /ተጠሪዎች መልስ እና ማስረጃቸውን በሬጅስትራር በኩል ለ30/10/2014 ዓ.ም 8፡30 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በተጨማሪም ክስ ለመስማት

ለ04/11/2014 ዓ.ም 3፡30 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ንግድና/ኢ. ምድብ 1ኛ ባንክና ኢንሹራንስ ችሎት አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

**ንግድና ኢንቨስትመንት ቡድን**